# ከሸሕ ጦረኛ አንድ ወረኛ ትጥቅ ያስፈታል

## ህወሓት ነበር ጀነራል አበበ ተከለሀይማኖት በአቶ ገብሩ ላይ ያቀረበው የአሉቧልታ ዘመቻ

ግልፅ ደብዳቤ ለጀነራል አበበ ተከለሀይማኖትና ጀነራል ፃድቃን

ከባርናባስ ገብረማሪያም



ጀነራል ፃድቃን

በአንድ መንደር ከኔ በላይ ቆንጆና ጀግና የለም ብላ የምትመካ አንዲት ዝንጀሮ ነበረች። አንድ ቀን በመንገድ ላይ እየተንጎራደደች ስታልፍ ወደ ገበያ መደብር ጎራ ብላ ድንገት በግድግዳ ላይ የተሰቀለ ትልቅ መስተዋት ስትመለከት ፊትዋን ወለል ብሎ ታያት። የራሷን ተፈጥሮ መሆኑን አልገባትም ነበርና ቆም ብላ በመገረም ደጋግማ ስታየው "ወይኔ ጉዴ"!! ይህ አስቀያሚ መልክ የኔ ቢሆን ኖሮ አንገቴን በገመድ አንጠልጥዬ ታንቄ እሞት ነበር" አለች ይባላል። ( ከታሪክና ምሳሌ የንባብ መፅሐፍ የተወሰደ ሀገሪኛ አባባል)



ጀነራል አበበ

<<<<<<<<>>>>>>>>

**የ60 ሸሕ ታጋይ ሰማእታትን አደራ ጥሎ፣ ህዝቡንና ሀገሩን ለጅብ አስረክቦ፣ ለሆዱ ሲል በጥቅም ተንበርክኮ ከትግል ሜዳው የፈረጠጠው ጀነራል፣ እውነት ዛሬ የትግራይ ህዝብን ጠበቃ በመምሰል የገብሩ አስራትን "ጉድፍ" ለማየትና ለመተቸት ምን ያህል የሞራል መሰረት አለው።? >>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>**

የፅሑፌን መነሻ ጀነራል አበበ ተከለሃይማኖት ከጀነራል ፃድቃንና ከሌሎች ጋር በመተባበር ባልተገራ አንደበት፣ ሙያዊ ስነ ምግባርና ሃላፊነት በጎደለው አኳሃን በአቶ ገብሩ አስራት ላይ የከፈቱትን የቃላትና የስነ ልቦና ጦርነት አስመልክተው በትግርኛ ቋንቋ በዓይጋ ድሕረ ገፅ ላይ ያወጡትን በቂም በቀልና በተራ ስድብ ላይ የተመሰረተ የአሉቧልታ ፅሑፍን በሚመለከት ግልፅና አጭር የግሌን አስተያየትና ተቃውሞ ለመስጠት ነው።

ወደ ዋናው ፅሑፌን ከመግባቴ በፊት በቅድሚያ ለማሳሰብ የምፈልገው ቁም ነገር አለ። እሱም በአቶ ገብሩ አስራት መፅሐፍ ላይ ለምን ትችትና ተቃውሞ ቀረበበት ማለቴ እንዳልሆነ ላሰምርበት እፈልጋለሁ። ይሁን እንጂ በአንድ መፅሐፍ ላይ ትችትንና ግምገማን ለማቅረብ ቢያንስ ቢያንስ አንደኛ፣- በቂም በቀልና በጥላቻ የተመረዘና የተበከለ አእምሮ ሳይሆን ቅንነትን፣ ሚዛናዊነትንና ሃላፊነትን ይጠይቃል። በሌላ አነጋገር ነፃ ሕሊናንና ስብእናን የተላበሰ ሰው መሆን ይጠይቃል ማለት ነው። በሕብረተሰባችን ዘንድም ምንም ቢሆን ምንም የግል ጥቅምን ለሚሟላት ሲባል የገዛ ወንድሙን በሀሰት ምስክርነት አሳልፎ መሸጥ እንደ ነውር የሚታይ በጣም የተወገዘ ተግባር ነው። ሁለተኛ፣- ለፍትሕና ለዴሞክራሲ ቁሜያለሁ የሚል እውነተኛ ዜጋ የግለ ሰቦችን የመናገርና የመፃፍ መብትን ያበረታታል እንጂ በተፃፃሪ አይቆምም። ጉድለት ካለም የዜጎችን ስብእናንና ክብርን በማይጋፋ መልኩ በሰለጠነ መንፈስ እርምትንና ትችትን ያቀርባል እንጂ አካኪ ዘራፍ በማለት ያልሆነ ቀለም መቅባትና ሀቁን አጣምሞ ማቅረብ ነውር ነው። ሶስተኛ፣- ስህተትን በስህተት አይታረምም። በሀገራችን እስካሁን ድረስ ያለው የፓለቲካና የስልጣን ልምድ መለስ ብለን ስናየው የመጠፋፋት፣ የመጠቋቆር፣ የመደማሰስና አንዱ የሰራውን ሌላው ተነስቶ በተራው የሚያፈርስ እንጂ የተጀመረውን እንደ በጎ ተቀብሎ የራሱን ድርሻ ጨምሮ ገንቢና የተሻለ ሃሳብን የማቅረብ ልምድ የለንም። በዚህ ምክንያት አባቶቻችን በቀይ ደማቸውን ፅፈው ያወረሱንን ወርቃማ ታሪክ መጠበቅ አቅቶን እየዋለ እያደረ "<u>የእንቆቅልሽና ምን አውቅልሽ</u>" ታሪክ እየሆነ እንዲሄድ አድርጎታል። አራተኛ፣- ግለ ሰቦች በራሳቸው ተነሳሽነትና ወኔ ጥረው ግረው መስዋእትነትን ከፈለው የፃፉትን መፅሐፍ ለመተቸትና ለመቃወም በቅድሚያ መፅሐፉን ማንበብና በአግባቡ መረዳት ያስፈልጋል። መፅሐፉን ሳያነቡ ዝም ብለው በጥንቆላ መላምት በስማ በለው ፀሐፊውን መስደብና ማንቋሸሽ ግን ትዝብት ላይ የሚጥል ብቻ ሳይሆን ከስነ ምግባር ውጭ የሆነና ኢትዮጵያዊ ጨዋነትንም የሚያጎድፍ ወረዳ ተግባር ነው የሚሆነው።

ላለፉት 8 ወራት ገደማ በአቶ ገብሩ አስራት መፅሐፍ ላይ በተለያዩ ወገኖች ሲሰጡ የቆዩት በርካታ አስተያየቶችም እነዚህን መሰፈርቶች መሰረት አድርገን ስናያቸው ሁለት ገፀ ባህሪያቶችን እንመለከታለን። በአንድ በኩል በርካታ ሰዎች መፅሐፉን በበጎ መንፈስ በማየት ስነ ስርዓት በተከተለ መንገድ ያላቸውን አድናቆትና መልካም ምኞት ሲገልፁ ቆይተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የገዢውን ፓርቲ መሪዎችና

ሻዕቢያዎችን ጨምሮ አንዳንድ ግለሰቦች ከራሳቸው ፓለቲካዊና ቡድናዊ ጥቅም በመነሳት መፅሐፉን በህልውናቸው ላይ የመጣባቸው በማስመሰል በአቶ ገብሩ ላይ በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር የቂም በቀልና የጥላቻ ዘመቻቸውን ሲያካሄዱ ቆይተዋል አሁንም እያካሄዱ ይገኛሉ። ጀነራል አበበ ተክለሀይማኖት የህወሓት መሪዎች የእጅ አዙር የማጥቃት መሳሪያ በመሆን በቅርቡ በአቶ ገብሩ ላይ ያቀረበውን ሰፋ ያለ የአሉቧልታ ትችትም በዛሬው ፅሑፋችን ሰፋ ባለ መልኩ የምንዳስሰው ትልቁ ርእስ ነው። ወደ ዋና የጀነራል አበበ ነጥብ ከመተላለፋችን በፊት ግን ለመንደርደሪያ እንዲሆነን ቀደም ብለው በተሰጡት አስተያየቶች ላይ እንጀምራለን።

## በአቶ ገብሩ መፅሐፍ ላይ የቀረቡት ገንቢ አስተያየቶች

“ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ” የሚለው የአቶ ገብሩ አስራት መፅሐፍ ታትሞ ገበያ ላይ ከዋለ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ማንም ሳይገታው በራሱ ሂደትና ሀይል በመቶ ሸዎች እጅ ገብቷል። ቁጥራቸው የማይናቅ የገዢውን ፓርቲ ደጋፊዎችም ጨምሮ በርካታ ሰዎች ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን በተላበሰ አኳሃን ያላቸውን አድናቆትም ሆነ እርምት በተለያየ መልኩ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ አስተያየታቸውን ሲገልፁ ቆይቷል። መፅሐፉን አስመልክቶ በተለያዩ ድሕረ ገፆች፣ ራዲዮ ጣቢያዎች፣ ጋዜጣዎች፣ ሶሻል ሚዲያዎች፣ መፅሄቶችና ሳይበር ፓልቶኮችም ሳይቀር ትልቅ ቦታ፣ ከበሬታና ሽፋን በመስጠት መወያያና መማማሪያ ሆኖ መቆየቱ የሚታወስ ነው። እንዲያውም ብዙ ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ተነሳሽነት መፅሐፉን እየገዙ ለሌሎች ጓደኞቻቸው በመላክ፣ በማስተዋወቅና በማሰራጭት በአጭር ጌዜ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን ባሉበት የዓለም ዙሪያ ሁሉ በመጠኑም ቢሆን እንዲዳረስ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ከዚህም አልፎ አንዳንድ አንጋፋ ኤርትራውያን ሊሂቃንን ጨምሮ በርካታ ኢትዮጵያውያን ምሁራንም በራሳቸው ተነሳሽነት መፅሐፉን በእንግሊዝኛና በሌሎች ቋንቋዎች ተተርጉሞ ለብዙ ህዝብ መዳረስ አለበት በማለት አስተያየታቸውንና መልካም ፍቃደኝነታቸውን ለግሰዋል።

ህወሓትን ከነ ነብሷ ከመሰረቱትና በከፍተኛ አመራር ላይ የነበሩት አሁን ከድርጅቱ ተለይተው በተለያየ መልኩ በመታገልና በምርምር ስራዎች ላይ የሚገኙት አንጋፋ ታጋዮችና ምሁራን ውስጥም እነ ዶክተር አረጋዊ በርሄ፣ አቶ ተስፋይ አፅባሃ (ቻንቶ)፣ ግደይ ዘርኣፅዮንና ሌሎች በርካታ ህወሓት ነበር ታጋዮች ጨዋነትንና ስነ ምግባርን በተላበሰ መልኩ በመፅሐፉ ላይ ያላቸውን አወንታዊ አመለካከትና ለወደፊትም ተስተካክለው መካተት አለባቸው ያሉዋቸውን ተጨማሪ ሃሳቦችን በማቅረብ አድናቆታቸውን ገልፀዋል። በተጨማሪም በፈረንጆች አቆጣጠር በ2001 ዓ.ም የህወሓት አመራር ተፈረካክሶ ለሁለት ቡድን ከተከፈለ በኋላ ተለይተው ፀረ የአቶ መለስ ዜናዊ የቤተ መንግስት ቡድን  አቋም ይዘው ከወጡት ታጋዮች ውስጥም አብዛኛዎቹ በመፅሐፉ ላይ ያላቸው አድናቆት በኩራት በመግለፅ የእንኳን ደስ አለህ መልእክት በተለያየ መንገድ ለአቶ ገብሩ አስራት እንዳስተላለፉላቸው ይታወቃል።

አብዛኞቹ አስተያየት ሰጪዎች እንዳስቀመጡት መፅሐፉን በተለየ ሁኔታ ተወዳጅ፣ አነጋጋሪና አከራካሪ እንዲሆን ካደረጉት ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ አንደኛ፣- ግለ መሪዎችን ወይም ግለ ድርጅቶችን የሚያወድስ ሳይሆን ሀገርንና ህዝብን ማዕከል ያደረገ ነው። ሁለተኛ፣- ህዝቡ ማወቅ ያለበትን ሀቆችንና አንገብጋቢ ጉዳዮችን አበጥሮ በድፍረት ያስቀመጠ ነው። ሶስተኛ፣- በሀገርና በህዝብ ላይ የተፈፀሙትን ገመናዎችና ክሕደቶች አስመልክቶ ራሱ ፀሐፊውንም ጭምር ተጠያቂ በማድረግ በማያወላውል መልኩ ያለ ምሕረት ያስቀመጠ መፅሐፍ ነው። አራተኛ፣- መፅሐፉ ስላለፈው ታሪክ የሚያወሳ ብቻ ሳይሆን ለመፃኢ የሀገራችን ዕድል ወሳኝና ትውልድ ተሻጋሪ  የሆኑትን ጉዳዮች በማንሳት የመሰረተ ሃሳብ ማዕዝን ድንጋይ ዘርዝሮ አስቀምጧል። አምስተኛ፣- የብዕር አጣጣሉንና የአፃፃፍ ዲሲፕሊኑን ለየት ያለ ነው። መፅሐፉ ከሞላ ጎደል ከስሜታዊ፣ ከቂም በቀል፣ ከወገተኝነትና ጠባብ ቡድናዊነት አስተሳሰብ የፀዳ ሚዛናዊ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሌላው ቀርቶ ገብሩን እንደ ጠላት ለሚያዩት ባለስልጣናትና ህወሓት ነበር መሪዎችም እንኳን ሳይቀር በአክብሮት አንቱ እያለ ነው የጠቀሳቸው። ከገብሩ ጋር አብረው ከህወሓት ተለይተው የወጡ ግለ መሪዎችንም በተመሳሳይ ማንንም ሳይፈራ በታሪኩ ሂደት ላይ የነበራቸውን ስፍራና ሃላፊነት በአወንታዊ ጎኑም ሆነ በአሉታዊ ጉኑ ያላንዳች ምሕረት በግልፅ አስቀምጧል። ስድስተኛውና ዋናው ነጥብ ደግሞ ህዝቡ በፀሐፊው ላይ ያለው እምነትና አክብሮት ነው። ገብሩ የህወሓት/ማሌለት ታጋይ ሆኖ ለረጅም ጊዜ በከፍተኛ የአመራር ቁንጮ ላይ የነበረ ሰው ከመሆኑም በላይ የድርጅቱን በስታሊናዊ ምትሓት የተለወሰ አመለካከትን ሰብሮ በመውጣት የራሱ የሆነ የተለየ ሃሳብ ይዞ ስለ 90 ሚሊዮን ህዝብ ታሪክ ደፍሮ ሲፅፍ በህወሓት መንደር የመጀመሪያ ሰው መሆኑን ብቻ ሳይሆን የገብሩ አስራትን ዓቅምና እውቀት በቅርብ ለማያውቁት ወገኖችም ሁሉ አስደንቋል፣ አስደስቷል፣ አስገርሟልም። ከዚሁ እምነትና እይታ በመነሳት መፅሐፉን በውል ያነበቡት ሰዎች “የተቀበረና የተጣመመ ታሪክን የገለጠ፣ ወዲፊት ለሚመጡ ፀሐፊዎችንም ሆኑ አርቲስቶች እርሾ ሆኖ የሚያገለግል ከመሆኑም በላይ ትውልድን ከትውልድ ጋር የሚያስተሳስር ድልድይ ነው” ሲሉ ገልፀውታል። አንዳንዶቹ ደግሞ የገብሩ መፅሐፍ ፍርትንና ጥርጣሬን የሰበረ ተምሳሌት ነው ብለዋል። አንዳንድ ፓለቲከኞችም “መፅሐፉ የታሪክ ምስክር ብቻ ሳይሆን የትግል መሳሪያም ጭምር ነው” በማለት የገብሩን ታላቅነት አድንቀዋል።

## የህወሓት መሪዎች በአቶ ገብሩ መፅሐፍ ላይ ያካሄዱት ስም የማጥፋት ዘመቻ

አዎ! "ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" የሚለው የአቶ ገብሩ አስራት የታሪክ መፅሐፍ ሚሊዮኖች ኢትዮጵያውያንን እንዳስደሰተና እንደኰሩበት ሁሉ በተቃራኒው እነ ሻዕቢያ ፣ የነ ስብሓት ነጋ ቡድን፣ የመለስ ዜናዊ ራእይ ጠባቂዎች፣ ሌሎች የህወሓት መሪዎችና ካድሬዎቻቸው ሁሉ ያልጠበቁትና በህልውናቸው ላይ የመጣባቸው መርዶ አድርገው ስለቆጠሩት በጣም ደንግጧል፣ ተደነባብረዋል፣ ተቆጥተዋልም። በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ በተለይም ጉዳቸውን ጠንቅቆ በሚያውቀቸው የትግራይ ህዝብ ፊት ስለተጋለጡም ትልቅ ሐፍረት ተሰምቷቸዋል። የህወሓት መሪዎች በትግል የህይወት ዘመናቸውን ቀና ብሎ የሚያያቸውና ተደፍረው የማያውቁትን ያህል ዛሬ ግን ሊቀይሩትና ሊከላከሉት የማይችሉበትን ታሪካዊ ሽንፈትና ሐፍረት ደርሶባቸዋል። እንዲያውም እንደ ዕድል ሆኖ መፅሐፉ ታትሞ የወጣበትን ጊዜ የህወሓት 40ኛ የልደት በዓላቸውን በደመቀ ሁኔታ ለማክበር በከፍተኛ ደረጃ ሽር ጉድ የሚሉበት ዋዜማ አካባቢ ስለነበር እንድምታው ቀላል አልነበረም። ከዚሁ ስጋትና ቁጣ በመነሳት በአቶ ገብሩ ላይ ከተራ ሰድብ ጀምሮ እስከ መብት ጥሰት የሚደርስ ጥቃት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ያላንዳች ይሉኝታ ሲያካሄዱት የቆዩትን የስም ማጥፋት ዘመቻ  ምን ያህል መረኑን የለቀቀና እሬት እሬት የሚል እንደነበር ከዚህ በታች በከፊል የተጠቀሱትን አስተያየቶችና ትችቶች መመልከት ይቻላል:-

1. አቶ ስብሓት ነጋ "ገብሩ ይህን ዓይነት መፅሐፍ በማሳተሙ ራሱን በራሱ የመግደል ተግባር (suicidal) ፈፅሟል" ሲሉ በአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ የትግርኛ ክፍል ከጋዜጠኛ ገብረ ገብረመድህን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ በይፋ በራዲዮ ተናገሯል።
2. የህወሓት ከፍተኛ አመራር አባል የሆኑት ዶክተር አዲስ ዓለም ባሌማም እንደዚሁ "ገብሩ የፃፈው መፅሐፍ ለትግራይ ህዝብ ሳይሆን ሌላ ሐይልን ለማስደሰት የተፃፈ ነው።" በማለት ለአሜሪካ ድምፅ ራዲዩ የትግርኛ ክፍል ከጋዜጠኛ ግርማይ ገብሩ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ገልፀዋል።
3. ሻዕቢያውያንም "ገብሩ በኤርትራ ላይ ዳግም ጦርነት ያወጀ የጦር ወንጀለኛ ነው" ሲሉ በተለያዩ መድረኮቻቸው ደጋግመው ገልፀውታል።
4. የህወሓት አባላትና የነ ስብሓት ነጋ የቅርብ ወዳጆች የሆኑት መምህር ሙሉወርቅ ኪዳነና አቶ ናሁሰናይ በላይ የሚባሉት ድርጎኛ ካድሬዎችም በተመሳሳይ የባለስልጣናቱን ስም የሚያሞጉስ በአንፃሩ ደግሞ አቶ ገብሩን የሚያወግዝ ፅሑፍ አቅርቧል።

5. ጀነራል አበበ ተክለሀይማኖትም ከመሰሎቹ ጋር በቅንጅት አዘጋጅቶ በቅርቡ ባወጣው ባለ 60 ገፅ የትግርኛ ፅሑፉ ላይ በሰጠው ትችት "የገብሩ መፅሐፍ ቀይ መስመር ተላልፏል፣ የህወሓትንና የትግራይ ህዝብን ታሪክና ማንነት አንቋሽሿል፣ መፅሐፉ የትግራይ ህዝብ ጠላቶች የሆኑትን የውስጥና የውጭ ቀኝ አክራሪ ሐይሎችን ለማስደሰትና ቅቤ የጠጣ ዱላ ለማቀበል ሲባል የተፃፈ መፅሐፍ ነው" ብሏል። ዝርዝሩን አንድ በአንድ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

<u>አቶ ስብሓት ነጋ</u> :- አቦይ ስብሓት ገና መጽሐፉን ምን እንደሚመስልና ምን ዓይነት ይዘት እንዳለው አንድ ገፅ እንኳን ሳያነቡ በወሬ ሰምቻለሁ በማለት ከአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ የትግርኛ ክፍል ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ "ገብሩ አስራት ይህን መፅሐፍ በመፃፉ ራሱ በራሱ ሱሳይድ (suicidal) ፈፅሟል" ሲሉ በይፋ ተናግሯል። "ህወሓት ከጥዋቱ ጀምሮ ከሻዕቢያ ጋር የነበረው ግንኙነት በጥናት ላይ ያልተመሰረተ፣ የሀገራችንን ብሄራዊ ጥቅምና ህልውና ያላገናዘበ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ርቱዓዊ፣ ታሪካዊና ሕጋዊ መብት የጣሰና ሚዛናዊነት የሌለው ነው" የሚለው የአቶ ገብሩ አቋምም አቶ ስብሓት እንዲህ ሲሉ ተናግሯል። "ድሮ አባቶቻችን የገምባሌ ጦረኛ አስተሳሰብ ይዘው የፈፀሙትን ስህተት ዛሬም ገብሩ ልክ እንደነሱ ዳግም ስህተት ፈፅሟል። ገብሩ ሻዕቢያ እስከ መጨረሻ በጦር መምታት ነበረብን ብሎ መፃፉና መናገሩ የአባቶቻችን የገምባሌ አመለካከት የሆነ ትልቅ ስህተት ፈፅሟል። በበኩሌ ከኤርትራ ጋር ያደረግነው ጦርነት ትክክል አልነበረም። ለሰላም ቅድሚያ መስጠት ነበረብን። የባህር በር፣ ሉዓላዊነትና ብሄራዊ ጥቅሚ የሚለው የገብሩ አባዜም በበኩሌ አልቀበለውም። <u>ኢትዮጵያ በታሪኳ ከጅቡቲ በስተቀር በኤርትራ አካባቢ የባህር በር ኖሯት አያውቅም</u>" በማለት በቁጣ ስሜት ሃሳባቸውን ደምድሟል።

<u>ዶክተር አዲስ ዓለም ባሌማ</u>:- የህወሓት ከፍተኛ አመራርና የቻይና አምባሳደር የነበረው ዶክተር አዲስ ዓለም ባሌማም በበኩሉ በቅርቡ በአምስተኛው ዙር ሀገራዊ ምርጫ ሰሞን ከvoa ጋር በትግርኛና በአማርኛ በተደረገለት ቃለ ምልልስ በሁለቱ ቋንቋዎች ለአንድ ጋዜጠኛ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦችን አቅርቧል። በአማርኛ ቋንቋ ለቀረበለት ጥያቄ ለስለስ ባለመልኩ "አቶ ገብሩ ራሱ ተዋናይ ሆኖ ይሰራበት የነበረውን ድርጅት ተመልሶ ስህተት ነበር ብሎ መፃፉ ትክክል አይደለም። የፃፈውን መፅሐፍ እዚህ ግባ የማይባል ቢሆንም ምናልባት ለወደፊት በዝርዝር መልስ እስጥበት ይሆናል" በማለት ራሱን ሰማይ ጣሪያ ሰቅሎ በትዕቢት ገልፀዋል። በማግስቱ በትግርኛ ቋንቋ ለቀረበለት ተመሳሳይ ጥያቄ ግን ሲመልስ ጠንከር ባለመልኩ "አቶ ገብሩ የፃፈው መፅሐፍ ለትግራይ ህዝብና ትግሉ የሚጠቅም ሳይሆን <u>ሌላ ሐይልን ለማስደተ ብሎ የፃፈው ነው። አቶ ገብሩ የራሱ ሐሳብ የለውም የሌላ ሐይል አላማ ለማስፈፀም ወኪል ሆኖ የሚንቀሳቀስ ነው"</u> በማለት የማንቋሸሽ ሃሳብ በይፋ ሲሰጥ ተደምጧል።

<u>የመለስ ዜናዊ አደራ ጠባቂዎችና ጀሌዎቻቸው</u>:- የመለስ ዜናዊ ቡድን በነ አቶ ገብሩ አስራት ላይ ጥርሳቸውን መንከስና ጣታቸውን መቀሰር የጀመሩት ዛሬ ብቻ አይደለም። ልክ ህወሓት/ኢሕአዴግ የደርግን ስርዓት አስወግዶ በትረ ስልጣኑን ከጨበጠ ማግስት ጀምሮ መሆኑን ይታወቃል። ለምሳሌ አቶ መለስ ዜናዊ በራሳቸው አንደበት በአንድ ወቅት በስብሰባ ላይ በይፋ የተናገሩትን ንግግሩ ማየቱ በቂ ነው። በፈረንጆች አቆጣጠር በ2001 ዓ.ም በክፍፍሉ ጊዜ እነ አቶ ገብሩ አስራት በአቶ መለስ ዜናዊ የተጠራውን የመቀሌ የካድሬዎች ስብሰባ ረግጠው ከወጡ በኋላ በአዳራሹ ውስጥ ለቀረው ተሰብሳቢ ካድሬ ሲገልፁ "የነዚህ መሪዎች ሞጎደኝነት አሁን የተፈጠረ እንዳይመስላችሁ። ልክ አዲስ አበባ ተቆጣጥረን ሀገርን ማስተዳደር አሃዱ ብለን ስራ ስንጀምር የተፈጠረ እንቢተኝነትና እብሪተኝነት ነው። ነገር ግን ዛሬ ነገ ይሻል ይሆናል እያልን ሆድ ይፍጀው ብለን ይዘነው ቆይተናል። ዛሬ በራሱ ሂደት ፈንድቷል።" በማለት በቁጣ መንፈስ ሲናገሩ ተሰምቷል። ከዚያች ቀን ጀምሮ በተለይም "ትግላችን እንቀጥላለን" ብለው ዓረና ትግራይ ፓርቲን ከመሰረቱት ውስጥ እነ አቶ ገብሩ አስራት፣ ወይዘሪት አረጋሽ አዳነንና አቶ አውዓሎም ወሉን ጨምሮ የበርካታ ታጋዮችን ቅስም ለመስበር፣ አንገት ለማስደፋት፣ ከህዝብ ጋር ለማጣላትና ለማገለል ሲባል ያወረዱትን የስድብ ናዳ፣ ያካሄዱትን የስም ማጥፋት ዘመቻና የስነ ልቦና ጦርነት ቢሰላ ሰብአዊ ፍጡር ሊሸከመው ከማይችል በላይ ነው። ለምሳሌ አቶ መለስ ዜናዊ እስከ ሕልፈተ ቀናቸው ድረስ የነ ገብሩ አስራትንና የሌሎች የዓረና ታጋዮችን ስም የሚጠሩት ሕገ መንግስቱ የሰጣቸውን መብት ተጠቅመው ባወጡት ሕጋዊ ሰውነት ሳይሆን እንደ ጦር የሚወረወሩ የስድብ ቃላቶችን በመምረጥ " ጭቃ፣ ገለባ፣ እሾኽ አሜኬላ፣ የጥፋት መልእክተኞች፣ ጠላት፣ ፀረ ልማት፣ ወዘተ " በማለት በትግርኛ ቋንቋ ሲናገሩ በቀጥታ ከአንደበታቸው ይደመጡ የነበሩትና ትተውልን ያለፉ የትናንቱ ትዝታዎች ናቸው። ዛሬም የሳቸው ራእይ ወራሾችና አደራ ጠባቂዎች ነን የሚሉን መሪዎችና ጀሌዎቻቸው በአቶ ገብሩ መፅሐፍ ላይ የሚያካሄዱትን የጥቃት ዘመቻ ተጠናክሮ ቀጥለዋል። የያዙትን በትረ ስልጣን መከታ በማድረግ የተለየ ሃሳብ ያላቸውን ዜጎች ሁሉ መዝለፍ፣ ማሰፈራራት፣ ማዋከብና ማሳደድ እንደ ትልቅ ሙያና የአገዛዝ ጥበብ አድርገው በመውሰድ እየሰሩበት ይገኛሉ።

<u>በሻዕቢያውያን ዘንድም</u> የገብሩን መፅሐፉ የፈጠረው ቁጣና ያቀጣጠለው እሳት ቀላል አይደለም። የኢትዮኤርትራ ጦርነት ከተቀጣጠለ ጀምሮ የሻዕቢያን የስድብ ፕሮፓጋንዳ ያነጣጠረው በነ መለስ ዜናዊ ሳይሆን በነ ገብሩ አስራት ቡድን ላይ ነው። <u>"የታላቅዋን ትግራይ ህልሞኞች፣ ጦርነት ናፋቂዎች፣ የሉዓላዊነትና የባህር በር የሞተ አጀንዳ አራማጆች፣ እሳት ጫሪዎች</u>"፣ ወዘተ እየተባሉ በሻዕቢያውያን ዘንድ ከሚከሰሱት፣ ከወቀሱትና እንደ ቀንደኛ ጠላት ተደርገው ከሚታዩት ህወሓት ነበር መሪዎች አንዱ አቶ ገብሩ አስራትን ነው። ሌላ ቀርቶ የኢትዮኤርትራ ጦርነት በተፋፋመበት ወቅትና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አንዳንድ በትግርኛ የሚያዘጋጅዋቸው ፊልሞች፣ አጫጭር ድራማዎችና ካርቶኖች ላይ ሳይቀር በትግራይ ህዝብ ላይ ያላቸውን ንቀትና ጥላቻ እንደ ማሳያ አድርገው ከሚቀርፅዋቸው ገፀ ባህሪያት ውስጥ አብዛኛው ጊዜ አቶ ገብሩን ነው ። ለምሳሌ "ጠራሮ" በሚል ስም በትግርኛ የተዘጋጀ የሁለት ሰዓት ልበ ወለድ መሰል ድራማ ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ አቶ ገብሩን የተውኔቱን ዋና ገፀ ባህርይ አድርገው በመቅረፅ "በቢሮ ቁጭ ብሎ የታላቅዋን ትግራይ ካርታ ሲያዘጋጅ፣ ከዚያም የኤርትራን መሬት ቆርሶ ወደ ትግራይ እያካለለ ሲጨምር፣ ጦርነት ሲያውጅና ሲያዘምት፣ የጦር ሜዳ መነፅር ይዞ ቀይ ባህርን አሻግሮ ሲቃኝ፣ የኤርትራ ነፃነትን ዳግም ለመንጠቅና ዓሰብንም ለማስመለስ ብሎ ሰራዊት ይዞ ሲገሰግስ፣ በመጨረሻም በመንገድ ላይ በኤርትራ ሰራዊት ተሸንፎ ባዶ እጁን ይዞ ሲመለስ ያሳያል።"

እርግጥ ነው አቶ ገብሩ የልቡን ሰርቷል። የሉዓላዊነታችን ነገር ባለቤት ያጣ ጉዳይ እንጂ የሞተ አጀንዳ እንዳልሆነ በመፅሐፉ ህያው በሆነ መንገድ ቁልጭ አድርጎ በማስቀመጥ የወላጅ አደራ ሰነዱን በመፅሐፉ ቀምሮ ለዚሁ ትውልድ በማስተላለፍ ታሪካዊ ሐላፊነቱን ተወጥቷል። ከእንግዲህ ወዲህ የመታገሉና የመነሳቱ ሃላፊነት አደራ ተራካቢው ትውልድ እንጂ የአቶ ገብሩ አይሆንም። ቀደም ሲል የትግራይ ክልል አስተዳዳሪና የህወሓት/ኢሕአዴግ ከፍተኛ የአመራር አባል በነበረበት ጊዜም <u>"ኢትዮጵያን አብረን እንዝረፍ"</u> የሚል የሻዕቢያ ገደብ አልባ ፓሊሲ እንዲገታ በማድረግና እንዲሁም በፈረንጆች አቆጣጠር በ1998 – 2000 በተካሄደው እልህ አስጨራሽ የኢትዮኤርትራ ጦርነት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በመግታትና በኋላም ሻዕቢያ አከርካሪውን ተመትቶ ከሀገራችን እንዲወጣ በማድረግ የአመራር አባል ሆነው ትልቅ አስተዋፀዖ ከነበራቸው ሰዎች አንዱ ገብሩ መሆኑን ሻዕቢያዎችም ራሳቸው በሚገባ ያውቁታል።

ዛሬም "የሀገራችን ሉዓላዊነት ጉዳይ ያልተዘጋ አጀንዳ ነው" በማለት የኢትዮጵያ ህልውናና ሉዓላዊ ክብር ለመጠበቅ የዓረና/መድረክ የአመራር አባል በመሆን በግንባር ቀደምትነት እየታገሉና መስዋእትነትን እየከፈሉ ከሚገኙት ሚሊዮኖች ኢትዮጵያውያን ውስጥ አንዱ ገብሩ አስራት መሆኑን ሻዕቢያውያን በሚገባ ያውቃሉ። በዚህ ምክንያት ሻዕቢያውያንና በህወሓት አመራር ውስጥ የሚገኙት ወኪሎቻቸው በገብሩ ላይ ጥርሳቸው ከነከሱበት ቆይቷል። ዛሬም "መፅሐፉን በኤርትራ ላይ የታወጀ ዳግም ጦርነት" ብለው በመወንጀል ጣታቸውን በገብሩ ላይ ቀስረዋል። በተለያዩ አፍቃሬ ሻዕቢያ በሆኑት የኤርትራ መድረኮች የገብሩን መፅሐፍ በሚመለከት ለወራት ያህል እየደጋገሙ አውግዘውታል። አቶ ገብሩ አስራትን ቀንደኛ የኤርትራ ታሪካዊ ጠላት አድርገው በማቅረብ ያልቀባጠሩት ነገርና ያልጠቀሱት የስድብ ዓይነት አልነበረም።

<u>በትግራይ መንግስት ደረጃ</u>ም በአቶ ገብሩ መፅሐፍ ላይ የተደረገው ዘመቻ ቀላል አልነበረም። መፅሐፉ ገና በዲያስፓራ ታትሞ በሀገር ውስጥም ገና መሰራጨት ከጀመረበት በፊት በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖረውና በተለይም በ40ኛው የህወሓት ልደት በዓል ላይ

አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይፈጥር እንዴት መከላከልና ማሳጣት እንደሚቻል የሚመክሩ አጥቂ ቡድኖችን በማቋቋም ተንቀሳቅሰውበታል። ለምሳሌ ከበዓሉ ቀደም ብሎ በአዲስ አበባ ከተማ ባደረጉት የምርጥ ካድሬዎች ስብሰባ የመፅሐፉን ነገር ተነስቶ እንደ አንድ ነጥብ እንደተወያዩበት ጉዳዩን በቅርብ የሚያውቁት ሰዎች ገልፀዋል። በትግራይም በበዓሉ ዋዜማ በመቀሌ ከተማ በሚገኘው የሰማእታት አዳራሽ "<u>የህወሓትን ታሪክ እንጠብቅ (ታሪኽና ንዓቅብ)"</u> በሚል መፈክር በመታጀብ ተዘጋጅቶ ከ3000 ሰው በላይ ህዝብ በተገኘበት የተካሄደው ሲምፓዚዮም ላይ የመድረኩ የክብር እንግዶችና ታሪክ ነጋሪዎች በመሆን የቀረቡት አቶ አባይ ፀሐየ፣ አቶ ስብሓት ነጋና አቶ ስዩም መስፍን ሲሆኑ በውይይቱ ሂደት "ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" የሚለው የአቶ ገብሩ መፅሐፍም ከተሰብሳቢዎችም ሆነ ከመድረኩ መሪዎቹ ተነስቶ ክርክር ተደርጎበት እንደነበር ታውቋል።

በነ ስብሓት በኩል መፅሐፉን "ውሸት ነው" በማለት የገብሩን ስራ ለማጣጣል ሲሞኩሩ፣ በተሰብሳቢዎቹ በኩል ደግሞ በተለይም ከአንዳንድ ምሁራን ተቃውሞ ቀርቦ እንደነበር በስብሰባው የተሳተፉት ሰዎች ይገልፃሉ። ለምሳሌ ከተሰብሳቢዎቹ ውስጥ አንድ ምሁር በአቶ ገብሩ መፅሐፍ ላይ በባለስልጣናቱ በኩል የተሰነዘረውን ስም የማጥፋት ተግባር "ድሮ በትግራይ መሳፍንት መካከል የእርስ በርስ መበላላት እንደነበር ከኋላ ታሪክ ጋር በማያያዝ "በሃፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት ንጉሱ ካቢኔያቸውን ሰብስበው በየጠቅላይ ግዛቱ የመከላኪያ በጀት ሲመድቡ የትግራይ ጠቅላይ ግዛት ግን በበጀቱ መዝገብ ውስጥ አልነበረም። ንጉሱን ለምን የትግራይ ጠቅላይ ግዛት በበጀቱ ውስጥ እንዳልተካተተ ተጠይቀው ሲመልሱ "ትግራይ የመከላኪያ በጀት አያስፈልጋትም። ምክንያቱ መሳፍንቶቹ እርስ በራሳቸው ይጠባበቃሉ ብለው ተናግሯል" በማለት ሲናገር ቤቱን በሳቅና በጭብጨባ እንደቀለጠ በሲምፓዚዮሙ የተሳተፉት ሰዎች በአግራሞት ይገልፃሉ። የአስተያየት ሰጪው ምሁር አባባል እንደ ገባኝ "በትግራይ በመሪዎች መካከል የእርስ በርስ መበላላትና መበቃቀል አሁን በነ ስብሓት ነጋ ብቻ የተጀመረ ሳይሆን ከድሮ ጀምሮ ተያይዞ የመጣና የተወረሰ ባህል ነው" የሚል መልእክት ለማስተላለፍ የፈለገ ይመስለኛል። በመጨረሻም ህወሓቶች በገብሩ መፅሐፋ ተገፋፍተው ያዘጋጁትን ሲምፓዚዮም ላይ ይዘውት የመጡትን ስም የማጥፋት ዕቅድ ተሰብሳቢው ህዝብ "ግለ ሰቦችን ለማውገዝ አልመጣንም" በማለት በተነሳው ተቃውሞ ምክንያት እንዳሰቡት አልተሳካላቸውም።

## ጀነራል አበበ በአቶ ገብሩ ላይ ያቀረበው የአሉቧልታ ዘመቻ

የህወሓት መሪዎች የገብሩ አስራትን መፅሐፍ በሰከነ አእምሮ አንብበው በቀጥታ ራሳቸው በይፋ መልስ ለመስጠትና ለመገምገም ድፍረቱንና ሞራሉን አላገኙም። ስለሆነም ገብሩን በእጅ አዙር ለማጥቃት የመረጡት ስትራተጂ በሁለት አቅጣጫ ነው። በአንድ በኩል ደካማና አድር ባይ የሆኑትን ግለ ሰዎች በጥቅም በመደለል ታሪክን በማጣመምና በማንቋሸሽ በሬ ወለደ ብለው እንዲፅፉ ይገፋፋሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በንግድ ሰም ፍቃድ አውጥተው በግል የሚንቀሳቀሱትን ዘመድ አዝማድ ጋዜጠኞች፣ የመፅሔት አዘጋጆች፣ አፍቃሬ ህወሓት የሆኑትን ድሕረ ገፆችን በመደጎም በሌሎች ግለ ፀሐፊዎች ላይ ስም የማጥፋትና የማደናገር ስራ ላይ እንዲሰማሩ ያደርጋሉ። በቅርቡ በጀነራል አበበ ተክለሃይማኖት ስም "<u>ምስጋና ታግሎ በማታገል ለድል ላበቃን የትግራይ ህዝብ</u>" በሚል ርእስ በትግርኛ የቀረበው የስድብና የአሉቧልታ ፅሑፍም በአቀራረቡና በይዘቱ የውክልና ስራ መሆኑን በትችቱ ላይ የተወረወሩትን ቃላቶች፣ ሐረጎችና ዓረፍተ ነገሮች ራሳቸው ተናጋሪዎች ናቸው። የቀረበው ፅሑፍ ሁሉንም አንድ በአንድ ተርጉሜ ባቀርበው ደስ ባለኝ ነበር። ነገር ግን በትችቱ የሰፈሩት አብዛኞቹ ነጥቦች ዘር ከዘር ጋር ከማቃቃር ሌላ የሚሰጡት ትምህርት የሌላቸው ትርኪ ሚርኪ ስለሆኑ እነሱን በመተርጎም ጊዜዬንና ጉልበቴን በማጥፋት አንባቢያንን ለማሰልቸት አልፈለኩም። ስለዚህ በዛሬው አጭር ፅሑፌ የመረጥኩዋቸውን አንኳር አንኳር ነጥቦች ብቻ በማትኮር የተቻለኝን ያህል በአማርኛ ተርጉሜ አቅርቤያለሁ። በአንዳንድ ጥቅሶች ስር ለጉዳዩ አፅነዖት ለመስጠት ተብሎ የተቀመጡትን የግርጌ መስመሮች የራሴ ናቸው። ዝርዝሩንም እኖሆ ቀጥሎ ቀርቧል።

የፅሑፉ ርእስ በትግርኛ ፦ ምስጋና ነቲ ተጋዲሉን ኣጋዲሉን ናብ ዓወት ዘብፀሓና ህዝብ ትግራይ

በአማርኛ ሲተረጎም፦ ምስጋና ታግሎ በማታገል ለድል ላበቃን የትግራይ ህዝብ

ፀሐፊ ፦ በአበበ ተክለሃይማኖት (ጀቤ )

*"የአቶ ገብሩ መፅሐፍ ቀይ መስመር ተላልፏል፣ ገብሩ ተናዶ የትግራይ ህዝብን ትግል አናንቋል፣ መፅሐፉ የጥፋት መልእክት (Disaster) ነው፣ መፅሐፉ ከኔ በኋላ ሰርዶ አይብቀል የሚል መልእክት የያዘ ነው፣"* .........በማለት የጀነራል አበበ ፅሑፍ ወቀሳውን እንደሚከተለው ይጀምራል።

"የትግራይ ህዝብና የህወሓት የትግል ታሪክ መሰረት አድርገው እየተፃፉ ካሉት መፃሕፍቶች ውስጥ አንዳንዶቹን አንብቤ ነበር። ነገር ግን እንደ አጋጣሚም ሊሆን ይችላል አብዛኞቹ ለግለ ሰቦች ለማሞገስ ወይም ለማጣጣል ማዕከል አድርገው የሚፃፉ ናቸው፡፡ በአንፃሩ <u>የትግራይ ህዝብንና የህወሓት ታጋዮችን ሚና ግን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ያወርዱታል</u>፡፡ "ልዑላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጲያ" የሚለው የገብሩ መጽሓፍ ቀደም ብለው ያነበቡት ህወሓት ነበር ከፍተኛ መሪዎች የሚሰጥቱን አስተያየት ከሰማሁ በኋላ ግን በጣም ገርሞኛል፡፡

የሁሉም መንፈስና አስተያየት መፅሐፉ የጥፋት (disaster) መልእክት ያዘለ እንደሆነ ነው የነገሩኝ። "እየተናደድን ነው ያነበብነው" ብለውኛል፡፡ ሌሎቹም "ገብሩ ተናዶ የትግራይን ህዝብ ትግል አናንቋል" ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ "ከኔ በኋላ ሰርዶ አይብቀል ዓይነት ነው" ወዘተ ይላሉ፡፡ ...... የገብሩን መፅሐፍ ሳየው ቀደም ብለው በትግራይ ትግል (ገድል) ስም ከተፃፉት መፃሕፍቶች በላይ ርቆ በመሄድ ቀይ መስመር የተላለፈ ሆኖ ተሰምቶኛል፡፡ ይህ በመሆኑም ልክ እንደሌሎቹ ታጋይ ነበር ጓደኞቼ እኔም ውስጤን በጣም ሲቆረቁረኝ ቆይቷል፡፡

ይህ ገብሩ የፃፈውን መፅሐፍ አስመልክቶ ከበርካታ ተጋሩ ብዙ ጥያቄዎችንና ስጋቶችን ይነሱ ነበር፡፡ ይህንን ጥያቄ ያነሱ ሰዎች ደግሞ በአጠቃላይ የህወሓት ወዳጆች ቢሆንም በመፅሐፉ ምክንያት መደነጋገራቸውን ግን አልቀረም፡፡ "ምንድን ነው ጉዱ?" የሚል ስሜት ነበራቸው፡፡ የአንዳንዶቹ ጥያቄ እኔም ከገመትኩት በላይ ነበርና እንዲህ ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ "ህወሓት የሻዕቢያ ቡቹላ ነው ማለት ነውን?" ...."ህወሓት የሀገራችን ብሄራዊ ጥቅም አሳልፎ ሰጥቷል ማለት ነውን?".... "ዴሞክራሲና ህወሓት የማይገናኙ ሆድና ጀርባ ናቸው ማለት ነውን?"... "ራሱ ገብሩንም ጭምር የነበረበትን ትግል መለስና ስብሓት እንደፈለጉት የሚያሽከረኩሯችሁ ደደቦች ነበራችሁ ማለት ነውን?"... "የትግራይ ህዝብ ዝም ብሎ እንደ በግ እየተነዳ ይከተላችሁ ነበር ማለት ነውን?" ... "ገብሩ ኣስራት ፖለቲካዊ መሪ ብቻ ይመስለን ነበር ለካስ ትልቅ ወታደራዊ መሪም ጭምር ነበር" ወዘተ የመሳሰሉትን መሰረታዊ የትግራይ ህዝብ ትግልንና የማንነቱን ታሪክ ጥርጣሬ ላይ የሚጥሉ ጥያቄዎች ሲነሱ ቆይቷል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ገብሩ ሚስጢር አውጥቷል በማለት በንዴትና በቁጭት ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ የህወሓት ታጋይ የነበረ ሰው "ህወሓት እንደዚህ ዓይነት ድርጅት መሆኑን ባውቅ ኖሮ አልታገልም ነበር" ሲል ሌላው ደግሞ "እንኳን ወደ ትግል አልገባሁ" በማለት ይገልፃሉ።".........

....."ውራይና" የምትባል በትግርኛ ቋንቋ የምትዘጋጅ ብቸኛ የግል መጺሄት እከታተላለሁ፡፡ እንዲሁ ሳያት ጥሩ መፂሄት ትመስለኛለች፡፡ ወጣቶቹ በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲህ ማድረጋቸው በጣም ደስ ብሎኛል ፡፡ ይህንን መፂሄት ስከታተል "ሉኣላውነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" የሚለው መፅሐፍ በሚመለከት መምህር ሙሉወርቅ ኪዳነ የፃፈው አስተያየት ሳይ በጣም በሳልና ለማንበብ የሚገፋፋ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ "ሉኣላውነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" የሚለውን መፅሐፍ "እንዴት እናነበዋለን?" በሚል ርእስ ናሁሰናይ በላይ የጠቀሳቸውን መልክቶች አንብቤያቸዋለሁ፡፡ የሚገርም መልእክት ነው ያስቀመጠው ፡፡ በተጠቀሱት መልእክቶች መሰረት በጋራ ምን ማድረግ እንችላለን ብዬ ብዙ ነገሮችን ሳስብ ነበር፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማረያም ደሳለኝ በ40 ኛው ዓመት የህወሓት ልደት በዓል ዋዜማ በመቀሌ ተገኝተው የተናገሩትን ንግግር በጣም በጣም አስደስቶኛል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ለአቶ ሃይለማርያም ምስጋናዬን ማቅረብ እወዳለሁ። በመሆኑም የመንግስታችን መሪ ንግግር መስረት በማድረግ የታጋይ ነበር ገብሩ አስራትን መፅሐፍ በሚመለከት አስተያየት ለመፃፍ ወሰንኩኝ።" የጥቅሱን መጨረሻ።

ከላይ በቀጥታ ከጀነራል አበበ የትግርኛ ፅሑፍ ተተርጉሞ የቀረበው ጥቅስ እንዳየነው የጀነራሉን ትችት/ነቀፌታ ልክ እንደ አቶ ስብሓት ነጋ መፅሐፉን ያነበቡት ሰዎች ነግረውኛል ከሚል መነሻ የቀረበ የስማ በለው ሃሳብ እንደሆነ እንረዳለን። እንዲያውም ጀነራል አበበ ይህንን ትችት የፃፈው በራሱ ተነሳሽነት ሳይሆን የጠቅላይ ሚኒስትሩ አቶ ሀይለማሪያምን ንግግር መሰረት አድርጎ እንደሆነ ራሱ መስክሯል። ትችቱ የአንድ ግለሰብ የጀነራል አበበ ሃሳብ ብቻ አይደለም። ከላይ በጥቅሱ እንደተገለፀው የተሳተፉት አበበ ተክለሃይማኖት፣ ናሁሰናይ በላይ፣ መምህር ሙሉወርቅ ኪዳነና የውራይና መፂሄት አዘጋጆችም ጭምር በተሳተፉበት አጥቂ ቡድን ተቀነባብሮ የቀረበ የጋራ የፓለቲካ ዘመቻ እንደሆነ እንረዳለን። የጀነራል አበበ ትችትም እንዲህ በማለት ይቀጥላል........

" የገብሩ መፅሐፉ...ተቃዋሚዎች በትግራይ ህዝብ ላይ ለሚደደርሱት ጥቃት በቃል ደረጃ በትክክል ቢያስቀምጥም ቅሉ የትግራይ ህዝብን ከነዚህ ጠላቶች ጥቃት ለመከላከል ግን ገብሩ አስራት አንድ ነገር አላደረገም። ይህም ነገሩን ከበመርሳት ወይም ካለማወቅ አይመስለኝም።" "አቶ ገብሩ አስራት የትግራይ ህዝብ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ የመፃፊያ ብዕሩን ይሰበርበታል።" ....

....."የኢትዮጵያ ህዝብ የኢትዮኤርትራ ጦርነት ከተጀመረበት ቀን አንስቶ እንደተለመደው በጋለ ወኔ በመነሳሳት ልጆቹንና ንብረቱን በመስጠት በሁሉም መልኩ የተቻለውን መስዋእትነት በመክፈልና እስከ ጦር ግንባር ድረስ በአካል በመሄድ ለሰራዊቱ የሚያስፈልጉትን የሞራልም ሆነ የቁሳቁስ አቅርቦት በሚሟላት ተወዳዳሪ የሌለው ሚና ተጫውቷል። ......... ይህ የኢትዮጵያ ህዝቦች ተሳትፎ ገብሩ አስራት በመፅሐፉ ጥልቅ ስሜት (passionate) በሚያሳይ መልኩ ካሁን በፊት ብዙም ስማቸው የማይነሳ ህዝቦችን ስም እየጠቀሰ በሚገባ ገልፆታል። ጥሩ ነው ። ነገር ግን እንደ አጋጣሚ ሆኖ በጦርነቱ ግንባሮች አካባቢ የነበረው ህዝብ (ትግራይና ዓፋር) የላቀ ድርሻ ነበረው ብቻ ሳይሆን የተዋጊ ሰራዊቱን እግር እየተከተለ በመሄድ ሎጂስቲክስ፣ መረጃና ሌሎች ነገሮችን በማቅረብ ቀጥተኛ የጦርነቱን ተሳትፎና ተጠቂ የነበረ ህዝብ በመሆኑ እንደ ታሪክ ሊወሳለትና ሊዘመርለት ይገባ ነበር። ነገር ግን አልሆነም። ምክንያቱ አቶ ገብሩ አስራት የትግራይ ህዝብ ጉዳይ በሚሆንበት ጊዜ የመፃፊያ ብዕሩን ይሰበርበታል።" የጥቅሱን መጨረሻ።

ጀነራል አበበ ትችቱን በመቀጠል ገብሩንና የትግራይ ህዝብን ለማጣላት ያለመውን ድርሰት እንዲህ ይላል ....."የ1997ቱን ሁኔታ ባስታወስኩ ቁጥር በገብሩ ላይ ጥያቄ እንዳነሳ አድርጎኛል። በገብሩ መፅሐፍ ገፅ 349-350 ላይ የተጠቀሰው "የተቃዋሚዎች ፓርቲና

*ህዝብን ያልለየ ቅስቀሳ" የሚል ነው። በዚያን ጊዜ ሁኔታው እንደተለዋወጠ "ገብሩ ፀረ የትግራይ ህዝብ ቅስቀሳ የሚያካሂዱ የሚባሉት በተለይም ከናንተ ጋር ግንባር የፈጠሩ ሰዎች ቅንጅት ናቸው። እነሱ ያልዋሉበት ጉዳይ ከሆነ ደግሞ በይፋ አላደረግንም (Renounce) ብለው ይናገሩ:: በተለይም እናንተ የዓረና ሰዎች ጋዜጣ ስላላችሁ ለትግራይ ህዝብ ልትከላከሉለት ይገባል" አልኩት። ገብሩ ደግሞ "ኣይ መጀመርያ የድርጅታችን ህልዉና ነው የምናየው" ይለኛል። ነገሩ አልተረዳኝም ነበርና "የተኛው ድርጅት ነው?" ብዬ ጠየቅኩት:: "ዓረና" ሲለኝ ገረመኝ። ገብሩ በሉዓላዊነት ጥያቄ ላይ ብቻውን ከመለስ ጋር ይጋፈጥ እንደነበረ በመመሰል በተደጋጋሚ ሲያቀርብ ታይቷል። ተቃዋሚዎች በትግራይ ህዝብ ላይ ለሚደርሱት ጥቃት በቃል ደረጃ በትክክል ቢያስቀምጥም ቅሉ የትግራይ ህዝብን ከተቃዋሚዎች ጥቃት ለመከላከል ግን ገብሩ አስራት አንድ ነገር አላደረገም። ይህም ጉዳዩን በመርሳት ወይም ባለማወቅ አይመስለኝም።"* የጥቅሱ መጨረሻ::

ጀነራል አበበ ባቀረበው ትችት ላይ የአቶ ገብሩ አስራትን መፅሐፍ ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምና አቶ አዳርካቸው ፅጌ ጋር አባሪ ተባባሪ በማመሳል እንዲህ በማለት ጠቅሷል:: *"በ97ቱ ምርጫ አካባቢ ፀረ የትግራይ ህዝብ ያነጣጠረ እንቅስቃሴ ለመመራት ካስቻሏቸው ነገሮች ውስጥ የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምንና የአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ መፃሕፍት ናቸው:: እኔም መፃሕፍቶቹን አንብቤ ነበር። ስሜቱን (Trauma) እስካሁን ድረስ አልቀቀኝም ። የገብሩን መፅሐፍ ይዘት ምን እንደሚመስል ከሰማሁ በኋላም እንደገና ስሜቱን አገርሽቶብኝ በአእምሮዬ ብልጭ አለኝና "ነፃነትን የማያውቅ ነፃ ኣዉጪ" የሚለው በአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ የተፃፈ መፅሐፍ አግኝቼ አንብቤዋለሁ:: ሌላው ሁለተኛው መፅሐፍ ግን አላገኘሁትም አጣሁት። ሃሳቤን በዝርዝር ለማስቀምጥ እንዲመቸኝ ገብሩንና ኣንዳርጋቸው ፅጌን የሚያመሳስላቸው ጥቅሶች አስቀምጫለሁና የሁለቱን አንድነትና ልዩነት በማነፃፀር እያያችሁ ልዩ ትኩት ሰጥታችሁ እንደምታነቡልኝ ተስፋ አደርጋለሁ"* ..... የጥቅሱ መጨረሻ::

*ፀረ የትግራይ ህዝብ የሆኑት ቀኝ አክራሪ ተቃዋሚዎች እንደሚሉት "የእግዚኣቢሄር ሚስጢር በመፅሃፍ ቅዱፍ፤ የወያነ ሚስጢር ደግሞ በገብሩ አስራት መፅሃፍ ይገለፃል" እያሉ እንደሚጨፍሩ ከአሜሪካ የመጣ አንድ ወንድሜ ነግሮኛል"* ..... በማለት የጀነራል አበበ ፅሑፍ አቶ ገብሩ የትግራይ ህዝብ ሚስጢር አውጥቶ ለሌላ ባዕድ ህዝብ አሳልፎ የሰጠ በማስመሰል እንደሚከተለው ጨምሮ ይጠቅሳል

......"ከህወሓት ከተለዩ አንጃዎቹ ውስጥ አንዳንዶቹ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በተለያዩ ሚዲያዎች የድርጅታቸውን "ሚስጢሮች" በማውጣት የዓቅማቸውን ያህል የተቋሞቻቸው ስም ለማጥፋት ተንቀሳቅሷል። የገብሩ መፅሓፍም የዚሁ ተቀጥላ ነው:: መፅሐፉ ገብሩ ራሱንና አንድ ሁለት ከሚሆኑ ግብረ አበሮቹን በስተቀር የሌሎቹን የአመራር አባላት ስም በማሳጣትና በማሳነስ እንዲሁም የትግራይ ህዝብ ታሪክ በዜሮ በማባዛት ባዶ ሆኖ እንዲቀር አድርጎታል። ..... ከአሜሪካ የመጣ አንድ ወንድሜ በአቶ ገብሩ አዲስ መፅሐፍ ምን እየተባለ ነው፣ ምን ይወራል? ብዬ ስጠይቀው " መፅሐፉ ብዙ ሰው ይጠሏል፤ ብዙዎች የተደናገሩ፣ ጥያቄዎችና ጥርጣሬዎች ያላቸው አሉ" ብሎኛል። "መፅሐፉን በሚመለከት አንዳንድ ታቃዋሚ ሐይሎች ምን እንደሚሉ ልንገርህ" አለኝ:: "የእግዚኣቢሄር ሚስጢር በመፅሃፍ ቅዱፍ፤ የወያነ ሚስጢር ደግሞ በገብሩ አስራት መፅሃፍ ይገለፃል" እያሉ ይጨፍራሉ" ሲል ነግሮኛል።" ....

...."ገብሩ ሐቅ እንደ እሳት እንዳያቃጥለው በመፍራትና በመደበቅ በአንፃሩ እውነታውን እያዛባ በመፃፍ የትግራይን ህዝብ፣ የሰፊውን ታጋይና መሪዎቹን ታሪክና ስብእና እያንቋሸሸ ፅፏል። ሁላችንም የምንኮራበትንና የምንመካበትን ትግል እያንኳሰሰ ቆይቷል። አቶ ገብሩ ላኮረፈችና ለተቆጣች ነብሱን የሚያፅናና እየመሰለው የትግራይ ህዝብን እንደ ከሃዲ በመቁጠር በዓይነ ቁራኛ ለሚያዩት ቀኝ አክራሪ ሐይሎችን "ቅቤ የጠጣ ዱላ" ለማቀበል መሞኮሩ እንደ ገብሩ ከመሳሰሉት ሰዎች የማይጠበቅ አሳፋሪ ተግባር ፈፅሟል። ይሁን እንጂ የትግራይ ህዝብ ታሪኩን ጠንቅቆ የሚያውቅና የማንም ውዳሴና ቡራኬ የማይፈልግ ኩሩ ህዝብ ስለሆነ ገብሩ የትግራይ ህዝብን ታሪክ ለማጣጣልና ለመደበቅ ቢሞክርም ምናልባት ለጊዜው መደናገር ሊፈጥር ይችል ይሆናል እንጂ የጤፍን ያህል አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደማይችል እርግጠኛ ነኝ። ...... ድሮ የማውቀው ንፁህ ገብሩም በግል ጥላቻ ተገፋፍቶ በራሱ ላይ በተፈጠረበት ርእዮተ ዓለማዊ ግጭት ምክንያትና እንዲሁም ሻዕቢያን የሚያይበት የተዛባ መነፀር የወለደው ምክንያታዊ ያልሆነ ፍራቻ (Paranoia) ተደማምረው በአሻጥራዊ አስተሳሰብ ላይ እንዲጠመድ ጠፍረው የያዙት ይመስለኛል። ለራሱ ሐቅ ማስተማር የማይችል ሰው ዓይኑን እንደተደፈነ ሆኖ ዘላለም መኖሩ አይቀርምና።" ..... የጥቅሱን መጨረሻ::

.....*"የገብሩን መፅሐፍ "የኢሕአዴግ ሰራዊት ትክክለኛ የኢትዮጵያ ሰራዊት አይደለም" ብለው ለሚያምኑ ሐይሎች ለማስደሰት የተፃፈ ይመስለኛል። ገብሩ ይቅርና ያልነበረበት የዓድዋ ታሪክ፣ ራሱ የነበረበት ሂደትና ከአብራኩ የወጣ የተወለደበት ሕብረተሰብ ያደረገው ፀረ ደርግ ትግል እንኳን በሚገባ አልፃፈም።" (አበበ ተክለሀይማኖት)* ........... አቶ ገብሩን የታሪክ ተወቃሽ ለማድረግ ትችቱን እንደሚከተለው ያጠቃልላል:-

“በኢትዮኤርትራ ጦርነት ወቅት የቀድሞ ጦር አባላት ሀገራችን በተወረረችበት ጊዜ መሰለፋቸው የሚታወስ ነው። ነገር ግን እዚህ ላይ በጣም የገረመኝ ነገር ቢኖር አቶ ገብሩ በውጊያው ተሰልፈው የላቀ ተሳትፎና ሚና ከነበራቸው ሌሎች ተዋጊ ክፍለ ጦሮች በላይ ለአንድ የቀድሞ ጦር ስብስብ ክፍለ ጦር በተለየ መልኩ (Single out) ለማሞጎስ መሞኮሩ ነው። ገብሩ እንዲህ ብሎ ለመፃፍ የተገደደበት ምክንያት ደግሞ ዝም ብሎ የመጣለት ሃሳብ አይደለም:: አላማው “የኢሕአዴግ ሰራዊት ትክክለኛ የኢትዮጵያ ሰራዊት አይደለም” ብለው ለሚያምኑ ሐይሎች ለማስደሰት የተፃፈ ነው የሚመስለኝ።” ..........

......”ገብሩ የኢትዮጵያ ታሪክ ብሎ በመፅሐፉ ያስቀመጠው ሐተታም ወገንተኛ ነው። በፅሑፉ የሰፈረው ሐተታ ሲታይ አዲስ ነገር አይደለም። ያው መጠነኛ ለውጥ ታክሎበት ነው ያስቀመጠው እንጂ በመሰረቱ የገዢ መደቦች የራሳቸው በሆኑት ኣፈ-ቀላጤዎች የተፃፈ በተለይም በሀይለስላሴ ዘመን አንደኛ ዓመት ዩኒቨርስቲ የተማርነው ነው ታሪክ ተብሎ የቀረበው። ታሪክ እንደ ፀሐፊው ነው። ዓቅም ያለውና ስልጣን ያለው ይፅፋል። በህወሓት ውስጥ እየታየ ያለውም ይኸው ነው። የዓድዋ ጦርነት የኢትዮጵያ ህዝቦች በአጠቃላይ በተለይም ያካባቢው ህዝብ ለሉዓላዊነታቸው ሲሉ የከፈሉትን መስዋእትነት ነው መፃፍና መቅረብ የነበረበት። ገብሩ በሁለተኛ የዓለም ጦርነት ፀረ የኢጣሊያ የባዕድ ወረራ የነበረ የህዝቦች ተሳትፎም ቢሆን በመፅሐፉ ውስጥ በተወሰነ ቦታ በጨረፍታ ከተጠቀሰው በስተቀር መላ ህዝቡ የተሳተፈበትን ፀረ የኢጣሊያ ወረራ የነበረ ተጋድሎ በተሟላ መልኩ አልቀረበም። ገብሩ የታሪክ ባለሙያ ስላልሆነ ለምን በተሟላ መንገድ አልፃፍክም አልለውም። ነገር ግን በጣም የገረመኝ የገዢ መደቦችን ብቻ የሚያወሳ ታሪክ ገብሩም ራሱ በመፅሐፉ መድገሙ ነው። ለነገሩ የሚገርም አይደለም። ገብሩ ይቅርና ያልነበረበት የዓድዋ ታሪክ ራሱ የነበረበት ሂደትና ከአብራኩ የወጣ የተወለደበት ሕብረተሰብ ያደረገው ፀረ ደርግ ትግል እንኳን በሚገባ አልፃፈም።” የጥቅሱ መጨረሻ።

ጀነራል አበበ ተከለሀይማኖት ከላይ በጥቅስ መልክ የተቀመጡትን ሀሳቦቸንና ሌሎች የገብሩን ስም ሊያጠፉ ይችላሉ የሚላቸውን ከዚህ ከዚያም በስማ በለው የለቃቀማቸውን ተባራሪ ወሬዎችን እየቀጣጠለና እያጣቀሰ ያቀረበውን የቂም በቀል ትችቱን እንዲህ በማለት ይደመድማል:: .....“የፅሑፌን መደምደሚያ እንድትሆነኝ የመረጥኳት አንድ ጓደኛዬ የነገረኝን ገጠመኝ ልንገራችሁና ልሰናበት። በኢራን አንድ ሀብታምና የተከበረ ሰው መልከ-ጥፉ (ፍንጓ) የሆነች ሴት ልጅ ወለደና አድጋ ዓቅመ ሔዋን ከደረሰች በኋላ በመልኳ መጥፎነት ምክንያት የሚፈልጋት ወንድ በመታጣቱ ባል ሳታገባ ቆማ ቀረች ። በኋላ ባለፀጋው አባትዋ ልጃገረዲቱን ከአንድ ዓይነ ስውር ጋር ሊድራት ይወስናል:: ምክንያቱ ዓይነ ስውሩ መልኳን ስለማያይ ጥሎዋት አይሄድም ብሎ በማሰብ ነው። ከዚያም የሰርጉን ቀን ደረሰና ሰርገኛውም ሁሉ ተሰባሰበ። ለሰርጉ ተጠርተው ከመጡ እንግዶች አንዱ የዓይን ሕክምና ባለሙያ ስለነበር ሙሹራውን ዓይነ ስውር መሆኑን ከተገነዘበ በኋላ አዘነና ለሙሹሪቱ አባት “ጌታዬ መልካም ፈቃድዎ ከሆኑ ሙሹራን ዓይኑን ማከም እችላለሁና ይፍቀዱልኝ” በማለት ይጠይቃቿል። አባትዮውም “ዶክተር!! ያልተረዳህ ነገር አለ፤ ይህ ሙሹራ ዓይኑ የሚያይ ከሆነ ልጄን ጥሏት ስለሚሄድ ተወው እንደነበረው ዓይነ ስውር ሆኖ ይኑር አታክመው ” በማለት ሰውዬውን ታክሞ መዳን እየቻለ ነገር ግን ልጃቸውን ላለማፋታት ሲሉ ዓይነ ስውር ሆኖ እንዲኖር ተፈረደበት ይባላል። “ የጥቅሱ መደምደሚያ።

## አጭር መልስ ለጀነራል አበበ ተክለሀይማኖት

አበበ ተክለሀይማኖት “ሰው ምን ይለኛል” ሳይል ኢትዮጵያዊ ጨዋነት፣ ሙያዊ ስነ ምግባር፣ ሃላፊነት በጎደለውና ባልተገራ አንደበት እንደመጣለት ያስቀመጣቸውን የስድብ ትችቶች ላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ስንመለከት ይቅርና ከአንድ የነፃነት ታጋይ የነበረና የተማረ ሰው ቀርቶ ከአንድ ተራ ሰውም ቢሆን የማይጠበቅ አሳፋሪ ተግባር ነው:: ይህም የሚያሳየን ከማንም በላይ የተጋለጠውና የተዋረደው ገብሩ ሳይሆን ራሱ ጀነራሉን ነው:: የራሱን ስብእና፣ ማንነት፣ ዓቅምና ሞራል ምን ያህል የወረደ መሆኑን ለመረዳት ከላይ በጥቅሱ የተቀመጡትን ነጥቦች ማየቱ ብቻ በቂ ይመስለኛል:: ብዙዎቹ ጓደኞቼ ፅሑፉን እናነበውም ብለውኛል:: አንድ ሁለት ጓደኞቹ ደግሞ “አይ ጥሩ ነው እንኳን እንዲህ ብሎ ፃፈ ። ገብሩ ዕድለኛ ነው” ሲሉ ገልፀውልኛል:: እርግጥ ነው ጀነራል አበበ ራሱን ብቻ አይደለም ያዋረደው መላ የህወሓት መሪዎችንም ጭምር ነው:: ቀደም ሲል የህወሓት ሊቀ መንበር፣ ቀጥሎም የድርጅቱን ማእከላይ ኮሚቴና ፓሊት ቢሮ አባል ሆኖ ለረጅም ጊዜ የቆየው አቶ ሰብሓት ነጋ የገብሩን መፅሐፍ ሳያነብ እንዲሁ በስማ በለው ሲደነባበር የሰማ ሰው በሙሉ መሳቂያና መሳለቂያ እንዳልሆነ ሁሉ ዛሬም ጀነራል አበበ ተመሳሳይ ስህተት ሲፈፅም መታየቱ ሀገሪትዋን እየመሩ ያሉት ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? የሚል ጥያቄም እንድታነሳ የሚያደርግ ነው:: ነገር ግን ጀነራል አበበ የሌላ ሰው ስም ከማጥቆር ይልቅ መጀመሪያ የራሱን ታሪክና ማንነት ቢነግረን ኖሮ ያምርበት ነበር::

ከላይ በጥቅሱ ተተርጉሞ የቀረበው የጀነራል አበበ ሀሳብ ደጋግሜ ሳነብ ድሮ የማውቀውና የህወሓት መሪዎችን ባህሪይና ተፈጥሮ ጠንቅቆ የሚያውቅ ስሙን ለመጥቀስ ያልፈለግኩትን አንድ የትግራይ ተወላጅ ምሁር ከ10 ዓመት በፊት በአንድ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ሲናገር ያዳመጥኩትን ንግግር ያስታውሰኛል:: “የህወሓት/ማሌሊት መሪዎችና ካድሬዎቻቸው ሁሉ ሌላ አማራጭ መንገድ የማያውቁ በስታሊናዊ ጨካኝ አስተሳሰብ ተኰትኩተውና እንደ ዓሳራ ግመል ፊታቸውን ተሸብበው ያደጉ ናቸው:: መለስ ዜናዊም

ብልጥ ነው። ሆን ብሎ የህወሓት/ማሌሊት ሶፍት ዌር ፕሮግራም በጭንቅላታቸው ውስጥ የገጠመላቸው ስለሆኑ ከዚያ አጥር ወጥተው ሌላ ሰፋ ያለ ዓለምና ሳይንስ የሚያዩበት መነፅር የላቸውም። ቢተኩሱም፣ ቢነግሱም፣ ቢማሩም ያው ናቸው አይለወጡም። ቀደም ብሎ በአእምሮኣቸው ከተገጠመላቸው የሶፍት ዌር ፕሮግራም ውጭ ሌላ የሚያውቁትና የሚናገሩት ሰላማዊ ቋንቋ የላቸውም። ሁሉ ጊዜ "በለው ደምስሰው - ያዘው ልቀቀው" የሚሉት ቃላቶች ብቻ ናቸው የሚታዩባቸው። ሕግ አይገዛቸው፣ ባህል አይገዛቸው፣ ታሪክ አይገዛቸው፣ ሀይማኖት አይገዛቸው፣ ጊዜ አይለውጣቸው፣ ዕድሜያቸው ልክ አንድ ዓይነት መዝሙር እየዘመሩ ጭንቅላታቸውን በማሌሊታዊ ሰይጣናዊ አስተሳሰብ እንደተቆለፈ ያልፋሉ። በመሆኑም አሁን እየታየ ያለው ትልቁ አሳሳቢ ጉዳይ የህወሓት መሪዎችና ካድሬዎቻቸው በማሌሊት ሶፍት ዌር ፕሮግራም መደንዘዛቸው አይደለም ችግሩ። ነገር ግን ከጫካ ይዘውት የመጡት መድሃኒት አልባ በሽታ ወደ ሌሎች ክልሎችም በፈጣን ሁኔታ እየተዛመተ መምጣቱ ነው። ስለዚህ "ቤቱን ሳይቃጠል በቅጠል" እንደተባለው እኛም በተራችን ሳንታመም የመከላል ዘዴ መፍጠር አለብን" በማለት ያስቀመጠውን ቁም ነገር አዘል ንግግር አስታውሳለሁ። መጀመሪያ አነጋገሩን አናድዶኝ ነበር። በኋላ ግን ችግሩን እዋለ እያደረ በራሱ ሂደት ጋሃድ እየሆነ መጥቷል።

ልክ ሰውዬው እንዳለውም ጀነራል አበበና መሰሎቹ በገብሩ መፅሐፍ ላይ እያቀረቡ ያሉት ጭፍን ተቃውሞም ደጋግሜ ሳየው መነሻቸው ድሮ ህወሓት በጫካ በነበረበት ጊዜ የሚጠረጥራቸውን አባላቱ ለመመንጠር ሲል ይጠቀምበት የነበረው የግምገማ ዘዴ ነው። አሉታዊ ወይም የተለየ አመለካከት አላቸው ተብለው የሚጠረጠሩትን ታጋዮች "ለማሌሊት አልወገናችሁም፣ ፀረ ወያኔ ናችሁ፣ የያዛችሁት አመለካከት የትምክሕተኞች አመለካከት ነው፣ የመሳፍንት አመለካከት ነው፣ የያዛችሁት መንገድ የጥፋት መንገድ ነው፣ ወዘተ" እያለ ሲገመግምበት የነበረውን መስፈርት ዛሬም የገብሩን መፅሐፍ ለመገምገም የተጠቀሙበትን ስልትና አካሄድ በውል ሲታይ ተመሳሳይ ነው። የአንድ ዜጋ ሕገ መንግስታዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ ሙብት ማክበር ማለት ከአንድ የፓለቲካ ድርጅት ህልውና በላይ ክብር እንዳለው እነ ስብሓት ነጋና ጀነራል አበበ የጤፍን ያህል ግምት አይሰጡትም። ጉዳያቸውም አይደለም። ምክንያቱም የዓይን ብሌናቸው ስልጣናቸው እንጂ የዜጎች ነፃነትና ድህንነት አይደለምና። ስለሆነም ገብሩን የሚከሱበት ዋናው ምክንያት ለሀገርና ለህዝብ አስበው አይደለም። " መፅሐፍ ስትፅፍ ከሀገርና ከህዝብ ጉዳይ በላይ ለምን የህወሓት ታሪክ አላስቀደምክም? የህወሓት መሪዎች ታሪክ ለምን ከሌሎች ኢዮትጵያውያን በበለጠ አልፃፍክም? የህወሓት ገመና በአማርኛ ፅፈሕ ለምን ሌሎች ኢትዮጵያውን እንዲያውቁት አደረክ? የሉዓላዊነት ጉዳይ ቀደም ብለን የቀበርነውን የሞተ አጀንዳ እንደገና እያነሳህ ለምን ትውልድን ትቀሰቅሳለህ? የደደቢትን ታሪክ ትተህ ለምን የድሮ ነገስታትንና መሳፍንትን የሚያወሳ የኢትዮጵያ ታሪክ ብለህ ትፅፋለህ? የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰራዊት አባላት ነበር ለምን ከህወሓት ሰራዊት እኩል ጠቀስካቸው? ከህወሓት አመለካከትና ከትግራይ ድንበር ወጥተህ ለምን ቀይ መስመር ተላለፍክ? ወዘተ ከሚል ከማሌሊታዊ አክራሪ የደሮ አስተሳሰቦች የሚመነጩ ክሶች ናቸው።

እነ ስብሓት ነጋ፣ አዲስ ዓለም ባሌማ፣ ጀነራል አበበ፣ ጀነራል ፃድቃን እና እንዲሁም የነርሱ ዘመድ አዝማድና ተላላኪዎች የሆኑት እነ መምህር ሙሉወርቅ ኪዳነ፣ ናሁሰናይ በላይና ሌሎች በተለያየ መልኩ በአቶ ገብሩ መፅሐፍ ላይ የሰጡትን አስተያየት ተጠቃልሎ ሲታይ ምናልባት በተለያየ አፍ መነገሩ ካልሆነ በስተቀር በአቀራረቡ፣ በይዘቱና መልእክቱ ከአንድ ወንዝ የተቀዳ ነው። ጀነራል አበበም ራሱ በፅሑፉ መግቢያ ላይ እንዳስቀመጠው "ስለአቶ ገብሩ መፅሐፍ ተመካከረን ምን ማድረግ እንችላለን ብዬ ሰዎችን አነጋግሬ ነበር" ብሏል። ስለዚህ በአቶ ገብሩ መፅሐፍ ላይ የተካሄደው ዘመቻ የተቀናጀና የተባበረ ድርጅታዊ ስራ መሆኑን የአደባባይ ሚስጢር ነው። በመሆኑም በአቶ ገብሩ አስራት ላይ የከፈቱትን የተቀናጀ የስነ ልቦናና የስም ማጥፋት ዘመቻ ልብ ብለን ስንመለከተው የሁሉንም ድምር መልእክትና አላማ ምን እንደሆነ በሚከተሉት ጥቂት ነጥቦች ሊጠቃለል የሚችል ነው፦

1. የሁሉም አስተያየቶችና ትችቶች በድምር ሲታይ በመፅሐፉ ላይ ያተኮረ ሂስ ሳይሆን ጥላቻን፣ ቂም በቀልን፣ ዘርንና ምንቀኝነትን ማዕከል ያደረገ፣ በውሸት ላይ የተመሰረተ የአሉቧልታና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ነው። አላማውም ገብሩን ከሚወደውና ከሚሳሳለት ከትግራይ ህዝብ ጋር ለማጣላትና ለመነጠል ያለመ ነው። ለምሳሌ የጀነራል አበበ ተክለሀይማኖት ፅሑፍ ሆን ተብሎ የተቀናጀ የፕሮፓጋንዳና የቂም በቀል መልእክት መሆኑን የሚያሳየው ትችቱ ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከመጨረሻው አንዲት ቃል እንኳ ለምልክት ያህል የገብሩን መፅሐፍ በአወንታ የሚያነሳ ጨርሶ የለም። ፅሑፉና ትችቱ በስድብ ተጀምሮ በስድብ ያልቃል። ስለዚህ እነ ስብሓትና እነ አባይ ፀሐየ ራሳቸው በአደደባይ ደፍረው ለመናገርና ለመከላከል ያልቻሉትን ሃሳብ በሌላ አፍ እንዲነገርላቸው በማድረግ ጀነራል አበበን እንደ ድምፅ ማጉሊያ አድርገው ተጠቅበመውበታል። እሱም በበኩሉ መፅሐፉን እንደ ኢጋጣሚ ተጠቅሞ ገብሩን በማጥቃት ከሽማምንቶቹ ጋር መታረቂያና እጅ መንሽያ አድርጎ ተጠቅሞበታል።

2. የሁሉም አስተያቶች ድምር መልእክት በሙሰና የጨቀዩ፣ ጊዜ የጣላቸውና በህዝብ የተጠሉትን የህወሓት መሪዎችን የሞራል ካሳ (massage) ለመስጠት ነው። በሌላ አነጋገር የህወሓት መሪዎች በሀገርና በወገን ላይ የፈፀሙትን ክሕደት፣ ዝርፊያ፣ ወንጀልና የሙብት ጥሰት ጠንቀቀው ያውቃሉ። በዚህ ምክንያት የገብሩን መፅሐፉ የትግራይ ህዝብን ልብ ያሸፍታል። እኛንም በህዝብ ፊት አሜኔታ ያሳጣናል፣ ያጋልጠናል ብለው ስለስጉ ሃጢኣታቸውን ለመደበቅና ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት ነው። ስለዚህ የመለስ ዜናዊንና

የስብሓት ነጋን ገናናነት ከፍ አድርጎና አጉልቶ በማስቀመጥ ያለ ታሪካቸውና ያለ ስማቸው ለመስጠት የተደረገ ጥረት ነው። በአሁኑ ጊዜ በህወሓት መሪዎች አካባቢ እየታየ ያለው ዓይን ያወጣ ፀያፍ ተግባርም የስልጣን፣ የገንዘብና የሀብት ንጥቂያ ብቻ አይደለም። የታሪክ ሽምያም በሰፊው ተጣጥፏል። ልክ በፅሕፈት ቤታቸው ቁጭ ብለው ያልተማሩበትንና ያልደከሙበትን የማዕርግ ዲግሪ በገንዘበ መቸብቸብ እንደተጀመረ ሁሉ በተመሳሳይ መልኩ የሌላ ሰው ታሪክ እየነጠቁ፣ እያጣመሙና እየቀበሩ፣ በአንፃሩ ስለጌቶቻቸው በሬ ወለደ ብለው እያወደሱ በመፃፍ የራሳቸው ያልሆነ ካባ የሚያለብሱ እንዳሉ በውል እያየን ነው። የጀነራል አበበ፣ የመምህር ሙሉወርቅ ኪዳነና ናሁሰናይ በላይ እንቅስቃሴም ከዚሁ ተግባር የተለየ አይመስለኝም።

3. ሌላው የጀነራል አበበ ፅሑፍ ልበ ወለድ ፈጠራ መሆኑን የሚያሳየው አብዛኛው የፅሑፉን መነሻ የሚያደርገው "ሲሉ ሰማሁ፣ ደውለው ነገሩኝ፣ ወንድሜ ነገረኝ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ማረከኝ፣ ወዘተ ከሚል እንደ ለማኝ እህል ከዚህም ከዚያም በተባራሪ ወሬ የተለቃቀሙ ሃሳቦችን በቆርጦ ቀጥል የተሰራና በስሜት የተነዳ ትችት እንጂ የራሱን የሆነ በጉዳዩ ላይ ያተኮረ ምሁራዊ ግምገማና ትንተና አይደለም። አብዛኞቹ በፅሑፉ ውስጥ የተካተቱት ነጥቦች ካሁን በፊት በዜና መልክ በድምፅ ወያነ ትግራይ ራዲዮ፣ በዋልታ ኢንፎርመሽን ድህረ ገፅ፣ በዓይጋ ድሕረ ገፅ፣ እንዲሁም በሌሎች የመንግስት ሚዲያዎችና በህወሓት ልሳኖች ላይ ያነብብናቸውና የሰለቹን ወሬዎች አሰባስቦ ነው ልክ እንደ አዲስ ሀሳብ አስመስሎ ገብሩን ለማጥቃት የተጠቀመባቸው። አንዳንድ ታዛቢዎች እንደሚሉት ከሆነ ጀነራሉ ይህን ያህል በስሜት የተነዳ ፅሑፍ ለመፃፍ የገፋፋው ለህዝብና ለወገን አስቦ ሳይሆን "ገብሩ በመፅሐፉ ላይ ተገቢውን ቦታ አልሰጠኝም።" የሚል ቅሬታ እንዳለው ለጀነራሉ ቅርበት ያላቸው ሰዎች ይናገራሉ። አንዳንዱም "አብደ ል ወይም በገንዘብ ሰክሯል" የሚሉም አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የጀነራሉን ተግባር ከቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ሕልፈት በኋላ በተለይም በነ አቶ ስብሐት ነጋ ተነሳሽነት "ህወሓትን መልሶ ማጠናከር" በሚል ዕቅድ ቀደም ብሎ ከተጀመረው እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ነው የሚሉም አሉ። በዚሁ ዕቅድ መሰረት እነ ስብሓት ነጋ በቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው የተንቀሳቀሱበት አካባቢ ጀነራሎቹን ጨምሮ በተለያየ ምክንያት ከህወሓት የወጡትን ነባር ታጋዮች በማነጋገርና በማግባባት ቢቻል ወደ ነበሩበት ድርጅት እንዲመለሱ ማድረግ፣ ካልተቻለ ደግሞ በያሉበት ሁሉ የህወሓት ተባባሪና ደጋፊ ሆነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ ነው። በአዲስ አበባ ዩኒቨሪቲ በሕግ ፋክልቲ እየሰራ የሚገኘው ጀነራል አበበም ሉዓላዊነትና የባሕር በር በሚመለከት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይዞት ከነበረው አቋም 90 ዲግሪ በመታጠፍ ዛሬ በገብሩ አስራት ላይ አካኪ ዘራፍ ማለት መጀመሩ ብዙዎቹን አስቋል። ስለዚህ ጀነራል አበበ የዩኒቨርስቲውን ግቢ የህወሓት ጠንካራ ምሽግ፣ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መናሃሪያ፣ ዘመናይ ካድሬዎችን መፈልፈያና መፍለቂያ ለማድረግ ታጥቆ የተነሳ ነው የሚመሰለው።

4. የሁሉም አስተያየቶች ድምር መልእክት አቶ ገብሩ በመፅሐፉ ላይ በጥልቀት ያስቀመጣቸውን የኤርትራ መገንጠል፣ የኢትዮኤርትራ ጦርነት ተኰላሽቶ መቅረት፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም አሳልፎ ስለመስጠቱና የባሕር በር ማጣት፣ በህወሓትና በሻዕቢያ መካከል የነበረው ያልተጠናና ሚዛኑን ያልጠበቀ ግንኙነት፣ ወዘተ የሚሉትን ጉዳዮች ውሸት መሆናቸውን ለማስረገጥና አጀንዳዎቹም ዳግም እንዳይነሱ ከስመው እንዲቀሩ ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ ተረባርቧል። በተለይም ጀነራል አበበ በሻዕቢያ በኩል የቤት ስራ የተሰጠው ይመስል አቶ ገብሩን ለማጥቃት ሲል ካሁን በፊት ይዞት የነበረውን የሉዓላዊነት አቋምም ሳይቀር ገልብጦ ወደ ቆሻሻ ቅርጫት በመጣል ከኤርትራውያን በላይ ሆኖ ስለኤርትራ መገንጠል ሕጋዊነትን ለትግራይ ህዝብ ለማስረዳት ብዙ የባጡን የቆጡን ቀባጥሯል። እንዲያውም ይባስ ብሎ ከላይ በጥቅሱ እንዳያችሁት "*ገብሩ ሻዕቢያን የሚያይበት የተዛባ መነፀር የወለደው ፍራቻ* " በማለት ገብሩን "በሻዕቢያ ላይ ያለህን አቋም አስተካክል" በማለት ዝቷል። "ወይ ጉድ" መቼም ሻዕቢያዎች ዕድለኞች ናቸው። እንደነ ጀነራል አበበ የመሳሰሉትን ሳይጠሩ አቤት የሚሉት "ወዶ ገባዎች" ካገኙ'ማ ወደኋላ አይሉም ይጠቀሙባቸዋል።

5. ጀነራል አበበ ተክለሀይማኖት በመፅሐፉ ላይ የሰጠውን ትችት ስናይ ዋና ጉዳዮችን ወደ ጎን ትቶ ገብሩ እግረ መንገዱን በጠቀሳቸው ጥቃቅን ነጥቦች ላይ ነው የተንጠለጠለው። በመፅሐፉ ላይ የራሱ የሆነ አቋም ይዞ የሚከራከር ሳይሆን እገሌ ነገረኝ! እገሌ እንዲህ አለ! ከሚል በመነሳት በአሉቧልታ ላይ የተመሰረተ ጭፍን ውግዘት እንጂ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ከገብሩ መፅሐፍ በምን እንደሚለይ አላስቀመጠም። ለማስቀመጠም አልፈለገም ምክንያቱ ከባለስልጣናቱ ጋር ያላቱሙኛል፣ ትዕዛብት ላይ ይጡሉኛል፣ የሚላቸውን ጉዳዮች አልነካም። ስለዚህ ከመፅሐፉ ጋር ምንም ዓይነት ተያያዥነትና ግንኙነት የሌላቸው፣ ቅራኔ ቀስቃሽና ዘርን ከዘር ጋር የሚያቃቅሩ ቃላትንና ሐረጎችን ከዋናው የመፅሐፉን ይዘት እየቆረጠና መንጭቆ በማውጣት የራሱን ተፀራሪ ትርጉም እየሰጠ፣ የገብሩን መፅሐፍ ይዘትና መንፈስ በዘፈቀደ እየቀያየረ ለማደናገር ሞክሯል። በጣም የሚገርመው ደግሞ ቀደም ሲል በተለያየ ጊዜ ከገብሩ ጋር በግል በሻይ ቤት ያወሩትንና ከመፅሐፉ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ጨዋታዎችንም ሳይቀር እየለቃቀመ የመፅሐፉን መገምገሚ አድርጎ በመጠቀም በፅሑፉ ላይ አስፍሯል። ልብ በሉ!! ጓደኛ መስሎ እየቀረበ የገብሩን አፍ ጠባዊ ሆኖ ወሬን እየሸመተ እንደቆየ መገመቱ አያዳግትም። "በሬ ከአራጁ ጋር ይውላል" የሚባለው ተረት ይኸው ነው።

6. ጀነራል አበበና መሰሎቹ በአቶ ገብሩ ላይ ያቀረቡትን ክስ ተራ ውሸት መሆኑን ከሚያሳዩት አንዱ የተጋሩ ሚስጢር አውጥተዋል፣ የትግራይ ህዝብ ታሪክና ማንነት አንቋሽሸዋል፣ አጣጥሏል፣ ወዘተ እያሉ ህዝቡን በስሜት ለማነሳሳትና ለማቃቃር ዘመቻቸውን ሲያካሄዱት ከርሟል። ለመሆኑ በአቶ ገብሩ በመፅሐፉ ውስጥ የተጋሩ ታሪክ የተንቋሸሸበትና እንዲሁም ከትግርኛ ተናጋሪ በስተቀር ሌላው ኢትዮጵያዊ ማወቅ ያልነበረበት የወጣ ሚስጢር ምንድን ነው? በመፅሐፉ ውስጥ በየተኛው ምዕራፍና ገፅ ላይ ይገኛል።? የገብሩ መፅሐፍ እኮ በዋናነት ሀገርንና ህዝብን ማዕከል ያደረገ እንጂ የያንዳንዱ ዘርና ክልል ዝርዝር ታሪክ የሚያወሳ አይደለም። የያንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብና ክልል ታሪክ በተናጠል እንፃፍ ካልን ደግሞ በጀት ተመድቦለት የራሱ የሆነ ሰፊና ተቋማዊ ጥናት በተቀናጀ መልኩ የሚካሄድ ነው የሚሆነው እንጂ በአንድ ግለ ሰብ የሚከናወን ስራ አይደለም። ለወደፊቱ መደረግም አለበት ብዬ አምናለሁ። ስለዚህ የትግራይ ህዝብ ታሪክ አጣጥሏል አናንቋል የሚለው ተራ አሉቧልታ እንጂ እውነት አይደለም። የኢትዮጵያ ታሪክ ሲነሳ በተለያየ መልኩ የሁሉም ህዝብ ጉዳይ አብሮ ይነሳል። የሀገራችን ሉዓላዊነት ጉዳይ ማንሳት ማለት ሁሉንም የሚመለከት ጉዳይ ነው። ስለዴሞክራሲ ማንሳት ማለት ሁሉንም ዜጋ የሚመለከት የሙብትና የነፃነት ጥያቄ ነው። በሀገርና በህዝብ ላይ የተፈፀሙ ክሕደቶችና በደሎች በዝርዝር መፃፍ ማለት ሁሉንም ዜጋ የሚመለከተውና ማወቅም ያለበት ጉዳይ ነው። ስለዚህ የገብሩን መፅሐፍ የትግራይ ህዝብን ታሪክ ለብቻው ነጥሎ አጣጥሎና አንቋሽሾ የጠቀሰበትን ነጥብ በየተኛው ምዕራፍና ገፅ ይገኛል?

ስለዚህ ጀነራል አበበ የገብሩን መፅሐፍ ገልብጦ ወይም በተገላቢጦሽ ነው ያነበበው። ገልብጦ ማንበቡና አጣምሞ መተርጎሙ ደግሞ ሳያውቅ ቀርቶ በየዋህነት አይመስለኝም። የህወሓት መሪዎች የህልውናቸው ጉዳይም ስለሆነ የግድ ገልብጦ ማንበብና ገልቦጦ ማቅረብ ግድ ሆኖባቸዋል። በመፅሐፉ ውስጥ እንደተቀመጠው እውነቱን እንመስክር ከተባለ ግን የትግራይ ህዝብን ታሪክ ገብሩ ሳይሆን ያጎደፈው በተቀራኒው እነ መለስ ዜናዊ፣ እነ ስብሓት ነጋ፣ እነ በረከት ስምዖን፣ እነ ቴድሮስ ሐጎስና መሰሎቻቸው ሆን ብለው ያራከሱትን፣ የሸጡትንና ያጣመሙትን ታሪክ ነው ከተጣለበት የቆሻሻ ቅርጫትና ከተቀበረበት ጉድጓድ አውጥቶ በመፃፍ ዳግም ህይወት እንዲዘራ ያደረገው ገብሩ አስራት ነው። ይህ በተጨባጭ ምን ማለት ነው?

- ገና በጫካ በደደቢት በረሃ ጀምሮ "የኤርትራ ትግል ከየት ወዴት" በሚለው መፅሐፉ "ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት የተያዘች ሀገር ስለሆነች መገንጠል አለባት" እያለ የፈጠራ ታሪክን በትግርኛ ፅፎ ለመላ የህወሓት ታጋዮችና ለትግራይ ህዝብ ለማስተማር ብሎ የፃፈው መለስ ዜናዊ እንጂ ገብሩ አስራት አይደለም። የትግላቸው ባሌቤቶች ኤርትራውያን ራሳቸው እያሉ ነገር ግን የህወሓት መሪዎች ከሌሎች ኢትዮያውያን በተለየ መልኩ በሻዕቢያ ፊት ጎንበስ ቀና የሚሉበት ሚስጢሩ ምንድን ነው? የህወሓት መሪዎች ኢትዮጵያን የመሰለ ትልቅ ሀገርና ታላቅ ህዝብ እያላቸው ለምንድን ነው ኤርትራ ሲነሳ ልዩ ጥብቅና ያላቸው ይመስል ሳይጠሩዋቸው አቤት እያሉ ከኤርትራውያን በላይ በመሆን ሽር ጉድ ማለት የሚያዘወትሩ? ምናልባት "ባርነትን የለመድ በሕልሙ ድንጋይ ይሸከማል" እንደሚባለው ይሆን?

- እንደነ ፕሮፌሰር ተስፋፅዮን መድሃኒየ የመሳሰሉት አንጋፋ ኤርትራውያን ምሁራን የሻዕቢያ አካሄድ ኤርትራን ነፃ የሚያወጣ ሳይሆን ለአካባቢውም ጠንቅና የጥፋት መንገድ ነው በማለት "የኤርትራ የትጥቅ ትግል አበቃለት" በሚል ርእስ የፃፉትን መፅሐፍ ኤርትራውያን እንኳን ራሳቸው ሳይቃወሙ አቶ መለስ ዜናዊ ግን ከኤርትራውያን ከባለቤቱ በላይ ለኤርትራ ነፃነት ልዩ ተቆርቋሪና ጠበቃ ሆኖ ፀሐፊውን እንኳን በወጉ ሳያስፈቅድ መፅሐፉን በተቃራኒው ገልብጦ በራሱ ፍላጎት በመፃፍ የሻዕቢያን ሀቀኝነትና ፍትሓዊነት ለትግራይ ህዝብ ለማስተማር ሲሞክር የነበረ መለስ ዜናዊ እንጂ ገብሩ አስራት አይደለም። ጀነራል አበበም ልክ መለስ እንዳደረገው የገብሩን መፅሐፍ ፊቱን አዙሮ ገልብጦ ነው ያነበበው።

- የሻዕቢያን ተግባር ያወገዙ፣ የህወሓት በኤርትራ ላይ የወሰደው አቋምና የግንጠላ ርዕዮትን በመቃወም ሉዓላዊነታችን ይከበር ብለው ጥያቄ ለሚያነሱ ተጋሩ ሲያስር፣ ሲገድልና ሲያሰቃይ የነበረው ህወሓትና መሪዎቹ ናቸው።

- የኢትዮጵያን መበታተንና ውድቀትን የሚመኝና ኢትዮጵያውያንን ሲያደማ ከነበረው ድርጅት ጋር በመተባበር የኤርትራ ነፃነት እውን ለማድረግና የሻዕቢያን ህልውና ለመጠበቅ ሲባል የትግራይ ለጋ ወጣቶችን ወደ ሳሕል በረሃ እየላከ እንደ ኣሳት ራት በጦርነት ወላፈን እየተለበለቡ ያሞራ ሲሳይና የባዕዳን ነፃነት ማዳበሪያ እንዲሆኑ ያደረገ ድርጅት ህወሓትና መሪዎቹ ናቸው።

- ከነፃነት በኋላም በኤርትራ ምድር ለዘመናት ሲኖሩ የነበሩት ኢትዮያውያን በተለይም ተጋሩ እንደጠላት እየተቆጠሩ ለዓመታት ያፈሩትን ሀብታቸውና ንብረታቸው እየተዘረፉ ባዶ እጃቸውና ባዶ እግራቸው እንደበግ እየተነዱ ሲባረሩ ጥብቅናና ከለላ ከመስጠት ይልቅ በእርምጃው ላይ ሲተባበሩና ሲደግፉ የነበሩት የህወሓት መሪዎች ናቸው። እንዲያውም አንዳንድ የህወሓት መሪዎች በግፍ የተባረሩትን ዜጎች ከማፅናናትና ከማስተናገድ ይልቅ "የኤርትራ ነፃነት ሲቃወሙና ሲሰሉ የነበሩት ናቸው፣ የከተማ ሌቦች የነበሩት ናቸው፣ የደርግ ሰራዊት ቤተሰብና ከደርግ ስርዓት ጋር ንክክ የነበራቸው ሰዎች ናቸው የተባረሩት" እያሉ በገዛ ወገኖቻቸው ሲያሾፉ የነበሩ ዛሬም በህይወት ያሉት የህወሓት መሪዎች ናቸው።

- “ኤርትራ የብቻችን ኢትዮጵያ የሁላችን” በሚል ፓሊሲና መፈክር ያላንዳች ገደብ የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብት በሻዕቢያ እየተቦረቦረ ወደ ኤርትራ እንዲሻገር በማድረግ አባሪ ተባባሪ በመሆንና እውቅና በመስጠት ህዝቡ ዓይኑ እያየና ኡኡ እያለ ሲጮኽ እየሰሙ እንዳልሰሙ መስለው የዝሆን ጆሮ በመስጠት ብሄራዊ ጥቅማችንን አሳልፈው ሲሰጡ የነበሩ የህወሓት መሪዎች ናቸው።

- ከነፃነት ማግስት ሻዕቢያ በቂም በቀል ተነሳስቶ ጠላቶቼ ናቸው የሚላቸውን ኤርትራውያንም ሆኑ ኢትዮጵያውያን ያላንዳች ሕጋዊ መነሻ ከያሉበት እየለቀመና እያፈነ ወደ ኤርትራ ወስዶ ሲያጉራቸውና ደብዛቸው ሲያጠፋ በነበረበት ጊዜ በወንጀሉ አባሪ ተባባሪ በመሆን በገዛ ዜጎቻቸውን ለጅብ አሳልፈው ሲሰጡ የነበሩት የህወሓት መሪዎች ናቸው።

- የኢትዮኤራትራ ጦርነት ከመከሰቱ በፊት የኤርትራ ታጣቂዎች ወደ ትግራይ መሬት እየገቡ የነዋሪውን ሀብትና ንብረት ብቻ ሳይሆን ሰዎችንም ጭምር እያፈኑ በመውሰድ ሲገድሉና ሲያሰቃዩ በነበረበት ጊዜ የትግራይ ህዝብ “ሻዕቢያ ይወረናል፣ እባካችሁ አድኑን፣ ልጆቻችን እንዳላታገልን ሁሉ ዛሬ የሚደርስልን ወገን አጣን” እያለ በሻዕቢያ አለንጋ እየተገረፈ ሲጮኽና ሲያለቅስ በነበረበት ጊዜ ጆሮ ዳባ በማለት “የጣላ ቤት ወሬ ነው፣ ከሻዕቢያ ጋር ሊያላትሙን የሚፈልጉ የትምክሕተ'ች ወሬ ነው “ እያሉ በማጣጣል ህዝቡን ለወራሪ ሻዕቢያ ለጅብ አሳልፈው የሰጡት የህወሓት መረዎች ናቸው። ለዚህ ሁሉ ጥፋት ጠያቂም ተጠያቂም የለም።

- በሻዕቢያ ወረራ ጊዜም ሆነ ማግስት ጦርነቱ ተኰላሽቶ እንዲቀር በማድረግ ባድመ የኛ አይደለም ሰጥተን እንገላገል፣ በፍርዱ መሰረት ባድመን ለሻዕቢያ ሰጥተን ወደ ልማታችን እንዙር አለበለዚያ ማዕቀብ ይደረግብናል፣ እርዳታ አናገኝም፣ ወዘተ በማለት የትግራይ ህዝብ በማስፈራራት ለሆዱ ሲል መሬቱንና ሉዓላዊነቱን አሳልፎ እንዲሰጥ በመገፋፋት በየወረዳው ህዝቡን እየሰበሰቡ ሲጎተጉቱና ሲያስፈራሩ የነበሩት የህወሓት መሪዎችና ካዴሬዎቻቸው ናቸው። ህዝቡ ግን አልተንበረከከም።

- በኢትዮኤርትራ ጦርነት ጊዜ በጦር ሜዳ ያሸነፈውን መከላኪያ ሰራዊት ሽባ በማድረግ በሄግ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲሸነፍ አድርጎ ሲያበቃ ነገር ግን በወቅቱ የነበረ የህዝብ ተቃውሞ በረዶ ጨምሮ ለማቀዝቀዝ ሲባል ባድመ ለኛ ተሰጥቷል በማለት በአዲስ አበባ ሰልፍ አዘጋጅቶ ህዝቡን በባዶ ሜዳ እንዲፈነድቅ በማድረግ በአደባባይ የዋሹና በዜጎች ላይ የቀለዱ የህወሓት መሪዎች ናቸው። ለፈፀሙት ወንጀልም ዋሽተናል ይቅርታ ብለው እንኳን በይፋ አልጠቀየቁም።

- የህወሓት መሪዎች በህዝብና በሀገር ላይ የሚፈፅሙትን ገመና በዚህ ብቻ አላበቃም ዛሬም እነ በረከት ስምዖንና እነ ሰብሓት ነጋ ለህዝቡ ባላቸው ንቀትና ዝቅተኛ ግምት የተነሳ በአደባባይ በይፋ “ባድመም ሆነ ዓሰብ የኛ አይደለም፣ የሉዓዓዊነት ጥያቄ የጥቂት ጦርነት ናፋቂዎች ጥያዌ እንጂ የህዝቡ አይደለም ሰልችቶች ትቶታል፣ ኢትዮጵያ በታሪክዋ ከጅቡቲ በስተቀር የባህር በር ኖሯት አያውቅም፣ ከሻዕቢያ ጋር ያደረግነው ጦርነት ስህተት ነው፣ የአባቶቻችን ቧላቀር ሀርበኛዊ የገምባሌ ስህተት ነው የደገምነው” ወዘተ እያሉ ሲያሾፍብንና ሲቀልዱብን ይታያሉ። ነገር ግን ማን ደፍሮ ይጠይቃቸው።

ይህ ከሆነ ሐቁ!! ከላይ በከፊል የተዘረዘሩትን የሀገራችን ብሄራዊ ጥቅም፣ ሉዓላዊ ክብራችን፣ ህልውናችን፣ ዳር ድንበራችንና ማንነታችንን የሚዳፈሩ ተግራባትን በሀገርና በህዝብ ላይ ወንጀል የፈፀሙ መሪዎች የሚመለከት በመፅሐፍ ማስፈር ማለት የትግራይ ህዝብን ታሪክና ማንነት ማንቋሸሽ ማለት ነው ወይ? እውነቱን እንናገር ከተባለ እኮ ለትግራይ ህዝብ ከህወሓት በላይ የሚቀርበውና መድህኑ 90 ሚሊዮኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። በተግባርም ታይቷል። በኢትዮኤርትራ ጦርነት ጊዜ ቆፎውን እንደ ተነካ ንብ ተነሳስቶ በመድረስ የትግራይ ህዝብን ከጠላት የጅብ ምንጋ ያዳነው መለስ ዜናዊ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። ስለዚህ የተኛው ሚስጢር ነው ማን ከማን የሚደባበቀው።? በህወሓት መሪዎች ላይ የሚቀርበው ክስ እንዴት ብሎ ነው የትግራይ ህዝብ ሃጢኣት ተደርጎ የሚወሰደው?

7. ጀነራል አበበና መሰሎቹ ገብሩ አስራትን ከትምክሕተኞች ጋር እንዳበረና የትግራይ ህዝብ ጠላቶችን ለማሰደሰት ተብሎ መፅሐፍ እንደፃፈ ይከሳሉ። ልብ በሉ!! እነርሱ ራሳቸው ከነ ኦነግ እና ከነ ሻዕቢያ ጋር ቁጭ ብለው የሽግግር መንግስት ሲመሰርቱ፣ የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ነን እያሉ ከነ አባ ዱላ፣ አዲሱ ለገሰና አቶ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ጋር ተሻርከው ሀገር ሲገዙ፣ አጋር ድርጅቶች እየተባሉ ከዓፋር ፣ ጋምቤላና ሱማሌ ከመሳሰሉት ድርጅቶች ጋር አብረው ሲሰሩ፣ እንዲሁም የኢሰፓና የደርግ ነበር ሽማምንቶችን በአማካሪነትም ሆነ በተለያዩ ሙያዎች ቀጥረው ሲያሰሩና አብረው ሲመዘብሩ በውል እየታየ ነው። ነገር ግን አንደነ ገብሩ አስራት የትግራይ ተወላጅ ሆነው ከሌሎች ሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ ተከትለውና ተደራጅተው ከሚንቀሳቀሱ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር በአደባባይ አብረው ሲቆሙ ግን እንደ ነውርና እንደ ወንጀል ተደርጎ እየተወሰደ የትምክሕተኞች መሳሪያ እየተባሉ በነ ጀነራል አበበና መሰሎቹ ሳይቀር እየተከሰሱ ይገኛሉ። ለመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ትምክሕተኛ የሚባለው ማን ነው? ድርጅት

ነው ወይስ ግለሰቦች ናቸው? ትምክሕተኛ የሚባለውስ የት ላይ ነው ድንበሩ? ትምክሕተኝነትስ ምንጩና መሰረቱ ምንድን ነው? በስልጣን ላይ ያሉት ህወሓትና መሰሎቹ ናቸው። የሀገሪትዋን ሁለመናዊ የኢኮኖሚና የልማት አውታሮች፣ የፓለቲካው ምሕዳር፣ መከላኪያንና ድሕንነት የተቆጣጠሩት እነርሱ ራሳቸው ናቸው። ስለዚህ ትምክሕተኛ ሊሆን የሚችለው ጉልበተኛው ነው ወይስ ደካማው ነው? በንጉሱ ዘመን የነበሩት ባለባቶችና ነገስታት የህልውናቸው መሰረት መሬት ነበር። የነበረው ስርዓትም ለነሱ የሚያዳላ ነበር። ከንጉሱ ሕልፈት በኋላ ግን ትውልድ ተቀያይሯል። የኢኮኖሚና የፓለቲካ መሰረቶችም ተቀያይሯል። ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ የትምክሕትንና የጠባብነትን ምንጭ ሊሆን የሚችለው የኢኮኖሚና የፓለቲካ መሰረት የተቆጣጠረው ሐይል ነው? ወይስ ባዶ እጅ ይዞ የቀረው ህዝብ ነው።? አቶ ገብሩ የዓረና መድረክ አባል ነው። መድረክ ደግሞ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦችን የተሰባሰቡበት ድርጅት ነው። ስለዚህ ማን ነው ለማን መሳሪያ ሆኖ የሚሰራው?

## ማጠቃሊያ

በበኩሌ ጀነራል አበበ ለምን በገብሩ መፅሐፍ ላይ ትችት አቀረብክ የሚል ጭፍን አመለካከት የለኝም። እኔም ራሴ ገብሩ ከፃፈው መፅሐፍ በተጨማሪ ሌላ የተለየ ሀሳብ ያለው ሰው ለመስማትና ለመማር እፈልጋለሁ። ገብሩ ሁሉም ነገር አጠቃልሎ ፅፈዋል የሚል እምነት የለኝም። አንድ ሰው የዓቅሙን ያህል ይፅፋል እንጂ ሁሉም ነገር ፅፎ ያመጣልኛል ብዬም አልጠብቅም። መሆንም አይችልም። እንደ ኢትዮጵያ የመሰለ ግዙፍና ውስብስብ ታሪክ ያለበትን ሀገር በሚመለከት ስህተትና ግድፈት የሌለበት ፍፁም የሆነ መፅሐፍ ይፃፋል ብዬ አሁንም ለወደፊቱም አልጠብቅም። ታሪክ የቅብብሎሽ ስራ ነው እንጂ በአንድ ትውልድ ብቻ የሚደመደም አይደለምና ። ስለዚህ ገና ለወደፊት አንዳንድ የተሳሳቱ ነገሮቸንም ካሉ አርመው፣ ገብሩ ያልደረሰበትንና ያላካተተውን የታሪክ ክንዋኔ ቀምረውና አጎልብተው የሚፅፉ ሽዎች የታሪክ ፀሐፊዎች እንደሚፈጠሩ ጥርጥር የለኝም። ጀነራል አበበም ብትሆን የፀሐፊውን ክብር፣ ሙብትና ማንነት በማይጋፋ መልኩ ሙያዊና ምሁራዊ ስነ ምግባር በተላበሰ አኳሃን በሰውዬው ላይ ሳይሆን በመፅሐፉ ዙሪያ የመሰለህን ሀሳብ ለመከራከር፣ ለመቃወምም ሆነ ለመደገፍ ማንም ሊገድበው የማይችል ሙሉ ሙብት እንዳለህ አምናለሁ። ነገር ግን አንተ ለመተቸትና ለመንቀፍ ሙብት እንዳለህ ሁሉ ሌላው ሰው ደግሞ የሕብረተሰቡን እሴት ጠብቆ ሀሳቡን በቃልም ሆነ በመፅሐፍ መልክ የመሰለውን ጉዳይ የመግለፅ ሙብት እንዳለው መቀበሉ አስፈላጊ ይመሰለኛል። ስለዚህ ፀሐፊም አንባቢም እኩል ሙብት አላቸው ማለት ነው።

ይሁን እንጂ አንድ ግለ ሰብ ራሱን ወክሎ፣ ራሱን ሃላፊነት ወስዶ፣ በራሱ እይታና ዕቅድ ጥሮ ግሮ የፃፈውን መፅሐፍ የሌላ ፓለቲካ ድርጅት አመለካከት እንደ መስፈርት አድርገህ መገምገም ትክክል አይመሰለኝም። ስለዚህ ጀነራል አበበ በገብሩ መፅሐፍ ላይ ያሳረፍከውን ትችት ለራስህ ነፃ ሰው ሆነህ በግልህ ያደረከው የአንባቢ አስተያየት ሳይሆን የህወሓትን አመለካከትና ርዕዮተ ዓለማዊ ፕሮግራምን መነሻ በማድረግ የሰጠኸው ድርጅታዊና የፓለቲካ ፕሮፓጋንዳ ግምገማ ነው። ስሜን ያለ አግባብ በመፅሐፉ ላይ ተጠቅሷል የሚል ሰው ወይም ድርጅት ካለ ራሱ ባለቤቱ መልስ መፃፍ ወይም መከራከር ይችላል። ጀነራል አበበ ግን የሁሉም ባለስልጣኖች ወኪል ሆነህ ነው መፅሐፉን የገመገምከው። ለምን እነርሱ ራሳቸው መልስ አይሰጡም።? ገብሩ የፃፈው መፅሐፍ በግሉ ነው። የማንም ፓለቲካ ድርጅት ወክሎ አይደለም። ሲፅፍም ለፓለቲካ ድርጅት ይጠቅማል ወይስ አይጠቅምም ብሎ አይደለም። ታሪካዊ ክንዋኔ ነው የፃፈው። የገብሩ መፅሐፍ የአንድ ፓለቲካዊ ድርጅት ታሪክ አይደለም። ስለዚህ ጀነራል አበበ መፅሐፉን ያየኸው ጠቅላላ ይዘቱን ሳይሆን በጭልፋ ነው። በመፅሐፉ ውስጥ የተጠቀሱትን ሌሎች ባህሪያት አያገባኝም ብለህ በሙተው ህወሓት የምትለዋን አንቀፅ ብቻ ጨልፈህ በመውሰድ ከሌሎች ባህሪያት ባልተገናዘበ መልኩ ሽራርፍህ በመፃፍ ለራስህ ተደናግረህ ሌላውን ሰው ለማደናገር ሞኩራሃል።

ከዚሁ እውነታ በመነሳት በጀነራል አበበና መሰሎችህ ላይ ያለኝን ተቃውሞና ጥያቄ፡- ልክ ትግራይ እናንተ ብቻ የተፈጠራችሁባት ይመስል ሌላውን ግን ለህገሩና ለህዝቡ የማያስብ ጠላት ወይም ሁለተኛ ዜጋ አድርጋችሁ በመፈረጅ ለምን ትሳደባላችሁ?። በስልጣን ላይ ያሉት የህወሓት መሪዎች ላይ የሚቀርበውን ወቀሳና ክስ ለምን ከህዝብ ጋር ታያይዙታላችሁ? በየተኛው የፓለቲካ ሳይንስና ሕጋዊ መለኪያ ነው ከ60 በላይ ፓርቲዎች ባሉበት ሀገር ላይ አንድ ድርጅት ለብቻው ተለይቶ ህወሓት ማለት የትግራይ ህዝብ ማለት ተደርጎ የሚወሰደው? የትግራይ ህዝብ እኮ ህወሓት ከመፈጠሩ በፊት የነበረ ባለታሪክ ህዝብ ነው። የትግራይ ህዝብ እኮ በጥቂት መሪዎች በስብሓት ነጋና በመለስ ዜናዊ አምሳል የሚቀረፅና የአንድ ድርጅት የግል ንብረት አይደለም። የ90 ሚሊዮን ህዝብ ሀብት ነው። ስለዚህ ጥቂት በሙሱና የተነከሩ፣ በሀገርና በወገን ላይ ግፍ የፈፀሙ መሪዎች ሲወቀሱ የትግራይ ህዝብ ተወቀሰ እየተባለ እስከመቼ እንኖራለን። ጥቂት መሪዎችን ከህዝብ በላይ አድርጎ ማየት ማለት እኮ ለታላቁ የትግራይ ህዝብ ድፍረት ነው። እውነት ጀነራል አበበ የሕግ ባለሙያና የፓለቲካ ተንታኝ ከሆንክ "ገብሩ የትግራይ ህዝብን ታሪክ አጣጥሏል፣ ረስቷል፣ አንቋሽሿል፣ ሚስጢር አውጥቷል፣ ክዷል፣ ከትግራይ ህዝብ ጠላት ጋር ወግነዋል፣ ወዘተ" እያልክ በፅሑፍ ደረጃ ያስቀመጥካቸውን ቅራኔንና ስሜትን ቀስቃሽ የሆኑት ቃላት መረጃህ ምንድን ነው።? እነዚህ ወንጀሎች በገብሩ መፅሐፉ ውስጥ በየተኛው ምዕራፍና ገፅ እንደሚገኙ ለምን አልጠቀስክም።? ስለዚ በስማ በለውና በጥላቻ መንፈስ ተነስተህ ለአንድ ሰላማዊና ለተከበረ ሰው የመንግስትን ጡንቻ ተጠቅማችሁ መሳደብ ግን ነውር ብቻ ሳይሆን ጋጥ ወጥነትንም የሚያሳይ ነው። መሳደብ አዋቂነት ወይም ጀግንነት ማለት ሳይሆን በሃሳብ፣ በሞራልና በፓለቲካ የከሰሩ መሪዎች

የራሳቸውን ገመናና ጉድፍ ለመሸፋፈን ሲሉ የሚጠቀሙበት የማምለጫና የመከላኪያ ስልት እንጂ የጤነኛ ሰው ባህሪያዊ መገለጫ አይደለም። "የዕብድ ገላጋይ ዱላ ያቀብላል ነውና።"

ለጀነራል አበበ አንድ ሁለት ተጨማሪ ጥያቄ ላቀርብና ፅሑፌን ወደ ማጠቃለሉ ልሸጋገር። ጀነራል አበበ!! እውነት የትግራይ ህዝብን ታሪክ ከገብሩ በላይ እናውቃለን፣ ጥብቅና እንቆማለን የምትሉ ከሆነና መፅሐፉን ትክክል አይደለም ተሳስቷል ብላችሁ የምታምኑ ከሆነ!! ህዝቡን በአሉቧልታ ፕሮፓጋንዳና በጥላቻ የቂም በቀል ዘመቻ ከማነሳሳት፣ ከማደናገር፣ ሌላ ሰው የሰራውን ስራ ከማጥቆርና ከማፍረስ፣ እንዲሁም በባዶ እጅ አካኪ ዘራፍ እያላችሁ ጊዜያችሁንና ገንዘባችሁን ከማባከን ይልቅ ለምን የበለጠ የታሪክ መፅሐፍ ፅፋችሁ ለሕብረተሰቡ አታቀርቡም።? በናንተ አመለካከትና እይታ "የገብሩን መፅሐፍ ውሸት ነው" ብላችሁ የምታምኑ ከሆነ ለምን ይህን ያህል ተንጫጫችሁ፣ ተናደዳችሁ።? የትግራይ ህዝብ የሚጠቅመውንና የማይጠቅመውን ለይቶ የማወቅ ብቃት፣ እውቀትና ሀይል አለው ብላችሁ በህዝቡ ላይ እምነትና አክብሮት ካላችሁ ለምን ህዝቡ ራሱ መፅሐፉን አንብቦ ውሸት ወይም እውነት ብሎ ፍርዱ እንዲሰጥ ነፃ አትለቁትም።? አንድ መፅሐፍ ታትሞ ገበያ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ እኮ የህዝብ ሀብት ነው እንጂ ለጥቂት ባለስልጣናት ተብሎ የሚፃፍ አይደለም። ጀነራል አበበ ያቀረበው ፅሑፍ ሳነብ በጣም የታዘብኩትና የገረመኝ ነገር አበበ በገብሩ ላይ ያለውን የግል ቅሬታ ደብቆ ነገር ግን በሌላ ሰው ላይ የተፈፀመ በደል አስመስሎ ነው ያቀረበው። ለምሳሌ *"ገብሩ የብአዴንን ታጋይ ጀግንነት ከሚገባው በላይ ስትጠቅስ ለምን የጀነራል ሳሞራ የኑስን የላቀ ጀግንነት አጉልተህ አልፃፍክም?"*..... ይላል በፅሑፉ። አያይዞም በመፅሐፉ ላይ አልተጠቀሱም ያላቸውን የሌሎቹ ባለሰልጣናትንም ስም በመጥቀስ ገብሩን ይከሳል። ይህንን አባባል ልብ ብለን ካየነው ሁለት ስለት ያለው ሰይፍ ነው። በአንድ በኩል ገብሩን የመንግስት ጡንቻ ካላቸው ሰዎች ጋር እያጣለው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ "ሌሎቻችሁም እንደኔ በገብሩ ላይ ዝመቱ" የሚል የፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ እያካሄደ ነው ያለው። መሆን የነበረበት ግን "ገብሩ በመፅሐፍህ ላይ ለምን እኔን በሚገባ አልጠቀስከኝም" ብሎ በግልፅ ብትጠይቅ ኖሮ ብለህነት ነው። ተጠቃልሎ ሲታይ ጀነራል አበበ የራሱን አቋም ሳይኖረው አንዴ የትግራይ ህዝብን ልዩ ተቆርቋሪ በመመሰል፣ በአንድ በኩል ከመፅሐፉ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ከተለያዩ ጋዜጦችና ድህረ ገፆች እየለቃቀመ በመለጣጠፍ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የባለስልጣናትን አፈ ቀላጤና ልዩ ውክልና የተሰጠው ፊትወራሪ በመምሰል የገብሩን ትልቅ መፅሐፍ በነፍጥ ለመለቅለቅ ሞክሯል።

ፅሑፌን በሚከተሉት ጥቂት ቃላት ላጠቃልል

ጀነራል አበበበ በቅርቡ በሚዲያ የለቀቀከውን የትግርኛ ፅሑፍ የሚያሳየው የአቶ ገብሩን ጉድፍ ሳይሆን ልክ ዝንጀሮዋ የራሷን ፊት በመስተዋት አይታ እንደ ገረማትና እንደ ደነገጠች ሁሉ የቀረፅከው አስቂኝ ድራማም የሚያሳየው ያንተን ኋላቀርነት፣ የሞራል ውድቀት፣ ክሕደትና መደነባባርን ነው። ምናልባት ገብሩን በማጥቃትና ያልሆነ ጥቅርሻን በመቅባት በህወሓት ባስልጣናቱ ዘንድ ርካሽ ተወዳጅነትና የጥቅም ፍርፋሪ ለማግኘት ስትል "የበግ ለምድ የለበሰ የቀበሮ ባህታዊ" በመምሰል በትግራይ ህዝብ ስም የፓለቲካ ቁማርን ለመጫወት አስበህ ከሆነ በጣም ተሳስተሃል። ሕብረተሰቡ እኮ እኔና አንተ ከምናስበው በላይ ብዙ ማይል ርቆ ሄዷል። እኔና አንተ ከምናውቀው በላይ ብዙ ጉድ ይታዘባል፣ ያውቃል፣ ይዘግባልም። በአሁኑ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ላይ ከአሉቧልታ ተነስተህ አቧራ በማንሳት ህዝቡን በስሜት መንዳትና ማታለል ፍፁም አይቻልም። ድሮ በደደቢት ዘመን ቀረ። በልቡ የሸፈተ የትግራይ ህዝብ ይቅርና የነ ጀነራል አበበ የድብብቆሽ ጨዋታ!! የጠቅላይ ሚኒተር ነበር የአቶ መለስ ዜናዊ የክተት አዋጅም የማይበገረው፣ ጠላቱንና የቀውጥ ቀን ወዳጁን ማን መሆኑን ጠንቅቆ የሚያውቅ ታላቅ ህዝብ መሆኑን ስገልፅ ውስጤን ትልቅ ኩራትና ወኔ እየተሰማኝ ነው።

ጀነራል አበበና መሰሎችህ ያልተረዳቸሁት አንድ ሐቅ አለ። ገብሩ ከእንግዲህ ወዲህ ኖረም አልኖረም የልቡን ሰርቷል። ገብሩ ማለት የሚሊዮኖች አመለካከትና አላማ ሆኗል። ገብሩ የዓረና/መድረክ አባል በመሆን በትግራይ ምድር የማይቻል ይምስል የነበረውን እንዲሚቻል ራሱን ተምሳሌ ሆኖ በተግባር አሳይቷል። ዛሬ በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር እየተካሄደበት ያለው ርብርብም ለገብሩ አዲስ ነገር አይደለም። ይህ አከራካሪ፣ የትግል ወኔ ቀስቃሽና አዲስ ምዕራፍ በር ከፋች የሆነውን መፅሐፉ ሲፅፍ የነ ጀነራል አበበ የፕሮፓጋንዳ ጥቃት ቀርቶ የህይወት መሰዋእትነት ዋጋም ሊያስከፍል እንደሚችል በመንፈስ ተዘጋጅቶበታል። እንዳሰበውም አላማው ተሳክቶለታል። ዛሬ የገብሩ መፅሐፍ በመቶ ሽዎች እጅ ገብቷል። ቢያንስ ቢያንስ አንዷን መፅሐፍ አንድ ገብሩ ወልዳለች። ገና ለነገይቱ ኢትዮጵያ ዘብ የሚቆሙ ሚሊዮኖች ታጋዮችንም ያፈራል። ስለዚህ ገብሩ ብቻውን አይደለም። ሚሊዮኖች ገብሩ በሀገር ውስጥም በዲያስፓራም አለን። ስለሆነም በዚሁ አጋጣሚ አቶ ገብሩ ታሪካዊ ሐላፊነትህን ተወጥተሃልና እናደንቃሃለን!! እናከብርሃለን!! እግዚአብሄር ካንተ ጋር ይሁን!! እኛም ከጎንህ አለን። !!!

ኢትዮጵያ በልጆቿዋ ተከብራ ለዘላለም ትኑር

ባርናባስ ገብረማሪያም ሐድጉ